# ሥልጡንሕዝብና ።

Democracy | Démocratie

## የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

http://www.slttunhzb.net ቍ.2011-002 ፥ ግንቦት ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ (May | mai 2019 A.D.) ። እ-ጦማር ፦ sh1@ttomar.net

ሥልጡንሕዝብና ፡ የተሠኘው ፡ መጽሔት ፥ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.)ን ፡ ተግባር ፡ ለማግራት ፣ ለማረማድና ፡ ለማስለጥ ፡ የቆመ ፤

- አንድነቱ ፥ ባሕርዩን ፣ ዐላማውን ፣ ፍልስፍናውን ፣ አሠራሩንና ፡ ውጤቱን ፡ ለይፋው ፡ የሚያሳውቅበት ፤
- ይፋው ፥ ሰው ፡ ሊሰማው ፣ ሊያውቀው ፡ ይገባል ፡ የሚለውን ፡ ማንኛውንም ፡ ሐሳብ ፣ ዜናና ፡ ድርስ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚገልጽበት ፥

ያንድነቱ ፡ ወቅታዊ ፡ መንግር ፥ የሕዝብ ፡ ምንባብ ፡ ነው ። መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፹ ፡ ዓ.ም. ፡ ባተ ።


## ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial

### የክዳት ፡ ቀን ።

---

ግንቦት ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ ኢትዮጵያና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በሸምጋይነት ፡ በቀረቧቸው ፡ ባሜሪካ ፡ መንግሥትና ፡ በግብር ፡ ዐበሮቹ ፡ ለንደን ፡ ላይ ፡ ተከዱ ። ይህች ፡ ቀን ፡ የክዳት ፡ ቀን ፡ ተብላ ፡ በታሪክ ፡ ስትታወስ ፡ ትኖራለች ።

ሽምግልና ፡ በባህላችን ፡ ክቡር ፡ ነው ። የክብረቱን ፡ መጠን ፡ ስንገልጥ ፡ *"ሰማይ ፡ ተቀደደ ፡ ቢሉ ፤ ሽማግሌ ፡ ይሰፋዋል!"* ፡ እንላለን ። ሰው ፡ ሌላን ፡ የሚያየው ፡ ራሱን ፡ በሚያይበት ፡ ዐይን ፡ ነውና ፥ አምነን ፡ ተከድተናል ፤ አይለምደንም ። ከእንግዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከራሱ ፡ በቀር ፡ ሽምጋይ ፥ ካገሩ ፡ ወዲያ ፡ ጉዳይ ፡ አይኖረውም ። ችግራችንን ፡ ራሳችን ፡ እንፍታ ፤ ጠላትንም ፡ መግቢያ ፡ ቀዳዳን ፡ እንንሣው ።

ከቶ ፡ ችግራችን ፡ ምን ፡ ቢኾን ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ እስካኹን ፡ ለመፍታት ፡ ያቃተን ፤ ለኀምሳ ፡ ዓመት ፡ -- ፡ ለመቶም ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፡ -- ፡ ካልፈታነው ፥ አገሪቱ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ጠንካራ ፡ ሥርዐት ፡ ቢኖራት ፡ ይኾን ፡ እስካኹን ፡ ያልፈራረሰችው ፤ የችግሩስ ፡ መነሻ ፡ ምን ፡ ይኾን ፤ ከውስጥ ፡ የመነጨ ፡ ወይስ ፡ ከውጭ ፡ የተቈሰቈሰ ፤ ወይስ ፡ ከኹለቱም ፤ ስለችግሩ ፡ ምንነት ፡ ስንመራመር ፥ ብዙዎቻችን ፡ የደረስንበትን ፡ ጭብጥ ፡ ስም ፡ ሳናወጣለት ፡ ኖረን ፥ ዛሬ ፡ *"ንጉልዮሽ"* ፡ ወይም ፡ *"nihilism"* ፡ ወደሚለው ፡ ልየታ ፡ አምርተን ፥ ሰፉ ፡ ያለ ፡ ስምምነትን ፡ አግኝተናል ። ንጉልዮሽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ያልተወሰነ ፥ ቀደም ፡ ሲል ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ተረማምዶና ፡ ተዛምቶ ፥ ጥንታውያን ፡ ሥልጣኔዎችን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ የተፈታተነ ፡ አጥፊ ፡ ኀይል ፡ ነው ። ከመንግሥታት ፡ ጥቂቶቹን ፡ እንደ ፡ ዩጎስላቪያ ፡ ሲደመስሳቸው ፥ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያሉትን ፡ ገፍትሮ ፡ ቢጥላቸውም ፥ አላሸነፋቸውም ። እንደ ፡ ቻይና ፡ ያሉቱ ፡ ደግሞ ፥ *"በተረቱበት ፡ ይረቱበት ፤ በተመቱበት ፡ ይመቱበት"* ፡ እንዲሉ ፥ የመጣባቸውን ፡ ዐጥፊ ፡ ኀይል ፡ በኀይልነቱ ፡ ገርተውና ፡ ጨብጠው ፡ ይዘው ፡ ተቋቁመውታል ። የባሰ ፡ ቢመጣባቸው ፥ ብቻቸውን ፡ እንደማይጠፉ ፡ አረጋግጠዋል ።

ሀገር ፡ ከወደቀበት ፡ የሚነሣው ፡ ቀድሞውኑ ፡ በቆመበት ፡ ሥልጣኔው ፡ ነውና ፥ ኢትዮጵያም ፡ በዚሁ ፡ አገባብ ፡ በሥልጡንሕዝብናዋ ፡ ዳግመኛ ፡ ተነሥታ ፡ ትቆማለች ❖

## ግልጽ ፡ ደብዳቤ ።

Open Letter | Lettre ouverte

ለንደን ፥ ግንቦት ፡ 01 ፡ ቀን ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

**ክቡር ፡ አቶ ፡ ሳጂድ ፡ ዣቪድ ፥**

**የብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ መጋቢ ፥**

**ሆም ፡ ኦፊስ ፥ ለንደን ፥ ታላቋ ፡ ብሪታንያ ።**

ክቡር ፡ ሆይ ፥

**የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፥** በለንደን ፡ ከተማ ፡ ከተቋቋመበት ፡ ከሐምሌ ፡ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፥ ኢትዮጵያን ፡ ከተፈራረቁባት ፡ የውንብድና ፡ አገዛዞች ፡ አላቅቆ ፡ ወደ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነት ፡ ለማሸጋገር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይታገላል ። ይህንም ፡ ሕጋዊና ፡ ሰላማዊ ፡ ትግላችንን ፡ ከብሪታንያ ፡ ብሔር ፡ ኾኖ ፡ ለመምራት ፡ ስለ ፡ ፈቀደልን ፥ መብታችንንም ፡ ስላከበረልን ፥ የብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ ለመቼውም ፡ የማንረሳውን ፡ ውለታ ፡ ውሎልናል ፤ ምስጋናችን ፡ ፍጹም ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ረዥምም ፡ የትግል ፡ ዘመን ፥ ብዙ ፡ ውጣ ፡ ውረዶችን ፡ አሳልፈናል ። ይህን ፡ ግልጽ ፡ ደብዳቤ ፡ ልንጽፍልዎ ፡ ያስገደዱን ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። በቀደሙ ፡ ዓመታት ፥ በተወሰኑ ፡ ሳተናዎች ፡ አባሎቻችን ፡ ላይ ፥ ከተርታና ፡ የማያቋርጥ ፡ ብቀታ ፡ አንሥቶ ፡ ለእንጀራቸው ፡ ከተቀጠሩበት ፡ ሥራ ፡ እስከ ፡ መባረርና ፡ ለ 25 ፡ ዓመት ፡ ከሥራው ፡ ዓለም ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ መወገድ ፡ የሚደርሱ ፡ ቀለል ፡ ከበድ ፡ ያሉ ፡ በደሎችና ፡ ጭቈናዎች ፡ በብሪታንያ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጽመውባቸዋል ። እነዚሁ ፡ አባሎቻችን ፡ በየግላቸውና ፡ በየጊዜው ፥ ከሚመለከተው ፡ የመንግሥት ፡ ዘርፍ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አንሥቶ ፡ እስከቀድሞ ፡ የሥራና ፡ ጡረታ ፡ መጋቢ ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ኢየን ፡ ዳንከን ፡ ስሚት ፡ (Ian Duncan Smith) ፥ እንዲሁም ፡ ያገር ፡ ግዛት ፡ መጋብያት ፥ ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ ቴሬዛ ፡ ሜይ ፡ (Theresa May) ፡ እና ፡ ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ አምበር ፡ ረድ ፡ (Amber Rudd) ፡ ድረስ ፡ መበደላቸውን ፡ የሚገልጹ ፡ አቤቱታዎቻቸውን ፡ በጽሑፍ ፡ አቅርበው ፡ ነበር ።

ኢ.ሀ.ሥ.አ.ም ፡ ቢኾን ፦

- *ናሽነል ፡ ዌስትሚንስተር ፡ ባንክ* ፡ (*National Westminster Bank*) ፡ ዘንድ ፡ ከፍቶት ፡ የነበረው ፡ የባንክ ፡ ሒሳቡ ፥ *"የባንክ ፡ ሒሳቡ ፡ አጠቃላይ ፡ መዝገብ ፡ ጠፍቶብናል"* ፡



©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በሚል ፥ ፍጹም ፡ የማይመስልና ፡ የማይገባ ፡ ምክንያት ፥ ድንገት ፡ በጉልበት ፡ ሲዘጋበት ፤

- እንዲሁም ፥ ሮየል ፡ ሜይል ፡ (*Royal Mail*) ፡ ዘንድ ፡ ተከራይቶት ፡ ከነበረው ፡ ፖስታ ፡ ሣጥን ፥ ደብዳቤዎቹ ፡ በተደጋጋሚ ፡ ተመዝብረው ፡ ሲጠፉበት ፥ አለዚያም ፡ ለላኪዎቻቸው ፡ አለምክንያት ፡ ተመልሰው ፡ ሲላኩበት ፥

አቤቱታዎቹን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደረጃ ፡ አቅርቦ ፥ ፍትሕ ፡ ቢያጣ ፥ ለእኛ ፡ ለአባላቱ ፡ ጥገኝነትን ፡ የሰጠ ፡ መንግሥትን ፡ ላላስቸግርም ፡ በማለት ፥ አንድነቱ ፡ የባንክ ፡ ሒሳቡንም ፡ የፖስታ ፡ ሣጥኑንም ፡ ርግፍ ፡ አድርጎ ፡ ተወ ። በምትኩ ፥ ዘመኑ ፡ ባመጣለት ፡ ዐዲስ ፡ የመገናኛ ፡ ዘዴ ፥ በኢንተርኔት ፡ መሥራት ፡ ዠመረ ። ኾኖም ፥ ብዙ ፡ ሳይቈይ ፥ ይህም ፡ ለስሙ ፡ "ነጻ" ፡ የተባለ ፡ የኢንተርኔት ፡ ዐቅም ፥ እየተጠለፈ ፡ ተሰነካከሎ ፡ የማያሠራው ፡ ኾነ ። አገልግሎቱን ፡ የሚያከራዩት ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶችም ፥ በኢንተርኔት ፡ መሥመሩ ፡ አሰናካዮች ፡ መኖራቸውን ፡ አምነው ፥ ራሳቸው ፡ ግን ፡ እንደሌሉበት ፡ ቢነግሩትም ፥ እስከ ፡ ዛሬው ፡ ዕለት ፥ አሰናካዮቹ ፡ እውስጣቸው ፡ ተሰግስገውም ፡ ኾነ ፡ ከውጭ ፥ መሥመሩን ፡ ሲፈልጉ ፡ እየከፈቱለት ፥ ሳይፈልጉ ፡ ደግሞ ፡ እየዘጉበት ፡ ተቸገረ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ መርበቢያችን ፡ www.slttunhzb.net ፡ ላለፉት ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ ሳይዘመን ፡ ከራርሟል ።

እነዚህ ፡ ድርጊቶች ፡ በማያጠራጥር ፡ ኹኔታ ፡ ሰብኣዊ ፡ መብታችንን ፡ ረምርመዋል ፥ አህጉራውያን ፡ ስምምነቶችንም ፡ በገቢር ፡ ሽረዋል ።

ኢ.ሀ.ሥ.አ.ም ፥ ለብዙ ፡ ዓመት ፡ በቃልና ፡ በደብዳቤ ፡ አቤት ፡ ሲልና ፡ ሲሟገት ፡ ቈይቶ ፥ ግፉ ፡ በፍጹም ፡ ማናለብኝነት ፡ እየበረታበት ፡ ስለ ፡ ኼደ ፥ ከእንግዲህ ፡ ትዕግሥቱ ፡ ከሞኝነት ፣ ይሉኝታውም ፡ ከጥፋት ፡ ሊቈጠርበትና ፥ ሥራው ፡ ሊበደልበት ፡ ኾነ ። እንሆ ፥ ጕዳቱ ፡ ቢብስበትና ፡ ሰሚ ፡ ቢያጣ ፥ የብሪታንያ ፡ መንግሥት ፥ ይህን ፡ በደል ፡ እንዲያስቈምለት ፡ በዚህ ፡ ግልጽ ፡ ደብዳቤው ፡ አቤቱታውን ፡ በትሕትና ፡ ያቀርብለታል ። ጕዳዩ ፡ በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጕዳይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ደግሞ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የሰብኣውያን ፡ መብቶች ፡ ብሔራዊ ፡ ድንጋጌ ፡ ባለቤቶች ፡ መላው ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ አቤቱታችን ፡ ለኹሉም ፡ እኩል ፡ እንዲደርስ ፡ ብለን ፡ በግልጽ ፡ ደብዳቤ ፡ ልናደርገው ፡ ተገደናል ።

ይህን ፡ በመሰለ ፡ ግፍ ፡ የብሪታንያና ፡ የኢትዮጵያ ፡ የቈየ ፡ ወዳጅነትና ፡ የጋራ ፡ ጥቅሞቻቸው ፡ እንዳይጐዱ ፡ በማሰብ ፥ ክቡርነትዎ ፡ ለጕዳዩ ፡ ተገቢውን ፡ ትኵረት ፡ እንደሚሰጠው ፡ እንተማመናለን ።

ካክብሮት ፡ ሰላምታ ፡ ጋራ ፤

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።

London, 8th of May 2019.

*(official translation of the Amharic original)*

**OPEN LETTER:**

**The Honourable Mr. Sajid Javid,**

**British Home Secretary, The Home Office, London**

Sir,

The **Ethiopians' Citizen Democratic Union** was established in London in July 1975, with the purpose of bringing about the transition of Ethiopia from dictatorial rule to that of democratic State of Right, and has been struggling to that effect ever since. Our gratitude to the British State for allowing us to engage in this lawful and peaceful struggle from their territory, is absolute; in so doing they have respected our most fundamental rights, and we the membership shall always remember this with a great sense of indebtedness.

During this long period of struggle, we have been through some difficult straits. The reasons that pushed us to write to you this open letter are numerous. Over the past years, some of our most active members residing in the United Kingdom had experienced here varying degrees of harassment and persecution, ranging from minor but constant administrative torments to more serious cases of dismissal from their wage earning jobs or even prevention from further employment which lasted for up to 25 years. The respective members had on their own behalf addressed their complaints in writing to their local area authorities in different times, and in the more serious recent cases, to the then Work and Pensions Secretary, the honourable Sir Ian Duncan Smith, and the successive Home Secretaries of the times, the honourable Mrs Theresa May, and the honourable Mrs Amber Rudd.

As for the E.C.D.U. itself:

- when the bank account it held with the *National Westminster Bank* was suddenly closed under the absolutely unbelievable and unjustifiable pretext that the bank had *"lost the records for the account"*;
- similarly, when letters and mail it was receiving through the Post Office Box it had rented from the *Royal Mail* were starting to be unlawfully mislaid and lost, or unnecessarily returned to their senders;


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

the E.C.D.U., having lodged its complaints at different levels, and finding no satisfaction for any one of them, resigned itself to relinquishing any of its claims, to avoid further inconveniencing the State that has in the first place offered safe haven to its members. Instead, it resorted to using the new means of communication that is the Internet. Sadly, our connections to this so-called "free" Internet were, here again, interrupted and hampered to a point where the new medium ended up being as useless. The Internet Service Provider acknowledged instances where signals were voluntarily obstructed, and that this was not of their doing; nevertheless those we can only describe as hostile elements in the ISP or elsewhere were opening and shutting the channel as they judge fit, with impunity. Thus, our website www.slttunhzb.net had remained non-updated for the past three years.

These acts have, in practice, trampled our basic human rights, and undermined international accords.

The E.C.D.U, had for so many years tried to settle these issues through verbal and written requests, only to find that the taunts merely intensified to a point where further patience would only be construed as mere credulousness, and further reticence as sheer recklessness, when its works were put in such grave danger. That is why, in desperation and for lack of any listening ear, it has finally decided, with great humility, to address its complaints to the British State with the hope that these persecutions will cease. As the matter concerns the Ethiopian people in the first instance, and all the signatory States of the United Nations' Universal Declarations of Human Rights in the second instance, we have decided to present our case in the form of an open letter, so that all concerned receive it.

We are confident that your excellency will give due consideration to this matter in order that the long-standing friendship and common interests between our two countries are not affected adversely.

Yours faithfully,

The Secretariat of the Provisional Executive Council,
E.C.D.U.

# መሠረቻ ፡ ጽሑፍ ።

## founding article | article fondateur

# የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፦ ሥልጡንሕዝብና ።

### የሥልጡንሕዝብና ፡ አመጣጥ ፡ በሀገረ ፡ ኵሽ ።

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

---

(ሥልጡንሕዝብና ፥ 3ኛ ፡ ዓመት ፥ ቍ.006 ፥ ነሐሴ ፡ 1985 ፡ ዓ.ም. ። )

እንዳገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪክ ፥ በተለይም ፡ ከምሁራን ፡ ማኅበር ፣ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ አደባባይና ፡ ከጨዋ ፡ ሸንጎ ፡ እንደሚሰማው ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፥ ጥንት ፥ በመሠረት ፥ ኻያ ፡ ስምንቱ ፡ አንጋደ ፡ ኵሽ ፥ አባታቸው ፡ እንደ ፡ ሞተ ፥ በሥልጣኑ ፡ ሊተካ ፡ የሚገባው ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ ያስተዳዳሪነት ፡ ተሰጥዎ ፡ የለውም ፡ ብለው ፥ አለው ፡ ያሉትን ፡ ሰባተኛውን ፡ ልጅ ፥ አቢስን ፡ መርጠው ፡ ሊሾሙ ፡ ሲነሡ ፥ በሥልጣኑ ፡ ሥያሜ ፡ ተጣሉ ። የሚያስማማቸውን ፡ አገባብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲጠበቡ ፡ -- ፡ "ፈልጉ ፡ ታገኛላችኹ" ፡ ነው ፡ -- ፡ አመቺ ፡ ኹኔታ ፡ አጋጠማቸው ።

ፈጣሪ ፡ የውሃ ፡ ጥፋትን ፡ እንዳነሣ ፥ ከኖኅና ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ የገባውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፥ ካም ፥ በብሔረ ፡ አዜብ ፡ በኖረበት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፥ በበኩሉ ፡ ለማደስ ፥ በያመቱ ፡ መፈጸሚያ ፡ ሰሞን ፥ እወንዝ ፡ እየወረደ ፡ ሲጠመቅ ፥ ምልክቱ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ በየቀኑ ፡ ጧት ፡ በፀሓይዋ ፡ ጨረር ፡ ከውሃው ፡ ሲነሣ ፥ ያምላኩን ፡ ቸርነት ፡ በይባቤ ፡ እያወደሰ ፥ አምልኮቱን ፡ በሰጊድ ፡ እያደሰ ፡ ቈይቶ ፥ የመዝክረ ፡ ዓምን ፡ (የመስከረምን) ፡ መባቻ ፡ በወግ ፡ በማክበር ፥ ዐላፊውን ፡ ዘመን ፡ ሸኝቶ ፥ መጪውን ፡ ይቀበል ፡ ነበር ። ልጆቹም ፡ አንጋደ ፡ ኵሽ ፥ ይህኑ ፡ አምልኳዊ ፡ ደኀኛ ፡ ልማድ ፡ አልተዉም ፡ ነበርና ፥ በዚሁ ፡ ወቅት ፣ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ እወንዝ ፡ ከትተው ፡ ተሰብስበው ፡ አሉበት ፡ ያስማሟቸው ፡ ዘንድ ፥ ብሶታቸውን ፡ ለነገድ ፡ አባቶቻቸው ፡ አመለከቱ ።

እነርሱም ፡ መክረው ፣ ዘክረው ፥ "እኹን ፡ እንዳደረጋችኹት ፡ ኹሉ ፥ ለወደፊቱም ፡ አሳዳሪያችኹን ፡ እናንተው ፡ በስምምነት ፥ ሲያስፈልግም ፡ በዕጣ ፡ ምረጡ ። ቀጥሎም ፥ ሊታመኗችኹ ፡ ባሕርያቸው ፡ የሚያስገድዳቸው ፥ ሊያውቁላችኹም ፡ ግንዛቦታቸው ፡ የሚፈቅድላቸው ፡ የነገድ ፡ አባቶቻችኹ ፡ መክረው ፣ ዘክረው ፡ የሚወስኑትን ፡ ሕግ ፡ አድርጎ ፥ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ ሳያበላልጥ ፥ በእኩል ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ እንዲያሳድራችኹ ፡ ተዋደዱ ፤ ከዚያም ፥ ውዴታችኹን ፡ የኹሉ ፡ ግዴታ ፡ አድርጎ ፡ እንዲያሳድራችኹ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

*ጠይቁት ። ሲቀበል ፥ ማስፈጸሚያውን ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሠይሙት"* ፡ ብለው ፡ መከሯቸው ። ምክራቸውን ፡ ወዶው ፡ ተቀበሉ ፥ ፈቅደውም ፡ ታረቁ ። ወዲያውም ፥ በኹላቸውም ፡ ስምምነት ፥ አቢስን ፡ ጠርተው ፥ ውዳቸውን ፡ አፍስሰው ፥ *"ታዲያስ ፥ ዐደራውን ፡ ልትቀበለን ፡ ትፈቅዳለኽን ፨ "* ፡ ብለው ፡ ሲጠይቁት ፥ ፈቃዱ ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጦላቸው ፥ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ በወግ ፡ አሰሩ ። በርሷም ፡ ጸጋ ፥ በእኩል ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ ወሰን ፥ በኹለት ፡ ፊት ፡ እታፈፈ ፥ በኹለት ፡ ፊት ፡ እኩል ፡ ተመዛዛኝነት ፡ እረጋ ፡ ዛጎን ፡ ላይ ፡ ያረፈውን ፡ ርትዐት ፡ ወይም ፡ የርትዕ ፡ ችሎት ፡ አሰፈኑ ። በርሱም ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ አዘዙ ፤ ሠለጠኑ ። ኻያ ፡ ስምንት ፡ አንጋደ ፡ ኰሽ ፡ የነበሩትን ፥ በፈቃዳቸው ፡ ተዋሕደው ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ አቢስን ፡ ኾኑ ። አቢስ ፣ አቢሴ ፣ አቢሳን ፡ ተባሉ ። ባንድነታቸውም ፡ የወል ፡ እግዚእናቸውን ፡ ተቀዳጅተው ፥ ሀገራቸውን ፥ ሀገረ ፡ ኰሽን ፡ በስማቸው ፡ አቢስያ ፣ አበሳንያ ፣ ሀገረ ፡ አቢስ ፡ አሠኙ ። የሚተዳደሩበትን ፡ ሕግ ፡ የሚመክርላቸውን ፡ ሀገራዊ ፡ የዐናት ፡ ሕዋስ ፥ በነገድ ፡ አባቶቻቸው ፡ ኅብረት ፡ "አ፞ባት" [1] ፡ ሠርተው ፥ ቀዳሚውን ፡ የርትዕ ፡ ዐልጋቸውን ፡ ዘረጉ ። ምርጣቸውን ፡ አቢስን ፡ ጠርተው ፥ "ሐፃኒ" ፡ ብለው ፡ አነገሡት ። በርሱም ፡ የመዠመሪያውን ፡ ሥልጡን ፡ መንግሥታቸውን ፡ አቆሙ ፤ ሠለጠኑ ። ለእግዚእናቸው ፥ በእግዚእናቸው ፡ ለሠሩት ፡ መንግሥት ፥ እኩል ፡ ዜጋው ፥ ታማኝ ፡ ሎሌው ፡ ኾነው ፡ ተገዙለት ፤ ሠለጠኑ ።

እንሆ ፥ እዚህ ፡ ድርስ ፡ ላይ ፥ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ በስምነቱ ፡ ተለይቶ ፡ አይጠራ ፡ እንጂ ፥ አቢሳን ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ሲያዙ ፥ ራሳቸው ፡ ለራሳቸው ፡ ሲታዘዙና ፥ አንዳቸው ፡ ለኹላቸው ፥ ኹላቸው ፡ ላንዳቸው ፡ ሲውሉ ፡ በሠለጠኑት ፡ እነርሱ ፥ ባካሉ ፡ ገዝፏል ፤ በግብር ፡ ውሏል ። ግብርም ፡ ለስም ፡ ያበቃል ፤ እንዲጠሩበትም ፡ ያስገድዳል ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ ግብሩ ፡ አጕልቶ ፡ ቀርጾ ፥ ለይቶ ፡ ባሳወቀው ፡ ስሙ ፥ ባለቤቱን ፡ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ ብለን ፡ ልንጠራው ፡ ይገ፞ባናል ።

ፍጡር ፡ የተፈጠረለትን ፡ ተግባር ፡ ማከናወን ፡ ባሕርያዊ ፡ ግዴታው ፡ ነው ። አቢሳን ፥ ጧት ፡ ሊለያያቸው ፡ የመጣባቸውን ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ ያስወግድላቸው ፡ ዘንድ ፥ የፈጠሩት ፡ አንድ ፡ ሕዝብ፞ናቸው ፥ ባንድነታቸው ፣ ላንድነታቸው ፡ እየሠራ ፥ ከቶ ፡ ማን ፣ ምን ፣ የት ፡ ተገኝቶ ፡ ይለያያቸው ፨ ምስጋን ፡ ለሥልጡን ፡ አንድነታቸው ፡ (ለሥልጡንሕዝብናቸው) ፥ እንደ ፡ ተመኙት ፡ ኹሉ ፥ አደጋውን ፡ አስወግዶ ፡ ከጥፋት ፡ አዳናቸው ።

*(ይቀጥላል ። )*

[1] አ፞ባት ፤ ("ባ" ፡ ይላላል) ፡ [አዘጋጅ] ።



# "ንጕልዮሽ" ፡ እና ፡ ማርከሻው ።

ክፍል ፡ 1/3 ፤

## ንጕልዮሽ ።

*ወሌ ፡ ነጋ ።*

---

የታሪኩ ፡ መነሻ ፡ ዘመን ፡ ከመራቁ ፡ የተነሣ ፡ ዕድሜው ፡ በትኽክል ፡ የማይታወቀው ፣ ሽማግሌው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፥ ነባር ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐቱና ፡ ደንቡ ፣ እምነቱና ፡ ባህሉ ፡ ኹሉ ፡ ከመጤዎች ፡ ፍልስፍናና ፡ ሥርዐት ፣ ደንብና ፡ ፈሊጥ ፣ ስግብግብነትና ፡ ነጣቂነት ፡ ጋራ ፡ ሲጋጩ ፥ ሀገሩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለታላላቅ ፡ ነውጦች ፡ ተዳረገች ፤ በ*"አብዮት"* ፡ የዐመፃ ፡ አዙሪት ፡ ውስጥ ፡ ድንገት ፡ ተወረወረች ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስም ፥ ካዙሪቱ ፡ ሰብሮ ፡ መውጣት ፡ ተስኗት ፥ ከማጡ ፡ ወደባሰው ፡ ዐዘቅት ፡ እየተንሸራተተች ፡ ስትወርድ ፡ እናያታለን ። ከቶ ፡ ለዚህ ፡ ውድቀት ፡ ለምንና ፡ እንዴት ፡ ተዳረገች ፨ ማንስ ፡ ዳረጋት ፨ እንዴትስ ፡ ተመልሳ ፡ ትወጣለች ፨ የሚሉት ፡ ጥያቄዎች ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ መተከዣዎቻችን ፡ ኾነዋል ። ለነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጥያቄዎች ፡ የተሟላ ፡ መልስን ፡ የሚሰጡ ፡ ሊቃውንት ፡ አይጠፉምና ፥ የማላገምረውን ፡ አልዠምርም ። ኾኖም ፥ እንደ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ ፥ *"ለዚህ ፡ ውድቀት ፡ ለምን ፡ ተዳረግን ፨ ማንስ ፡ ያወጣናል ፨ እንዴትስ ፡ ተመልሰን ፡ እንነሣለን ፨ "* ፡ ለሚሉ ፡ የተወሳሰቡ ፡ ጥያቄዎች ፥ አንድ ፡ የመልስ ፡ መዠመሪያ ፡ የምትኾን ፡ ማስታወሻን ፡ ለንባብ ፡ ማብቃቱ ፡ ተገቢ ፡ ስለ ፡ መሰለኝ ፥ የሚከተለውን ፡ በጽሑፍ ፡ አስፍሬያለኹ ። ይህን ፡ የመልስ ፡

መዠመሪያ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ይገልጸዋል ፡— "ንጉልዮሽ" ።

"ንጉልዮሽ" ፡ ላማርኛችን ፡ ዐዲስ ፡ ቃል ፡ ይመስለኛል ። ዐዲስ ፡ ቃል ፡ መኾኑም ፡ አይደንቅም ፥ ምክንያቱም ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የገጠማት ፡ አጠቃላይ ፡ ችግር ፥ ቀድሞ ፡ በታሪካችን ፡ ያልታየ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ዐዲስ ፡ መጠሪያን ፡ ጠይቋል ፤ ዐዲስ ፡ መፍትሔንም ፡ ይሻል ።

የ"ንጉልዮሽ" ፡ ዘር ፡ የግእዙ ፡ "ነጐለ" ፡ ባማርኛ ፡ "ፈረሰ ፣ ተናደ ፣ ረከሰ ፣ ተዋረደ ፣ ባዶ ፡ ኾነ" ፡ ማለት ፡ ሲኾን ፤ ከርሱ ፡ "ንጉል" ፡ ሳድስ ፡ ቅጽል ፡ ይገሰሳል ፡ ("የፈረሰ ፣ የተናደ ፣ የረከሰ ፣ የጠፋ ፣ ባዶ ፡ የኾነ" ፡ ማለት ፡ ነው) ። ፈረንጅኛ ፥ "null" ፣ "nil ፣ "nihil" ፡ ከሚለው ፡ ጋራ ፡ በድምፅም ፡ በትርጕምም ፡ ይስማማል ። ዘሩ ፡ የግእዙ ፡ "ነጐለ" ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ የሚል ፡ መላ ፡ ምት ፡ አለ ፤ ይመስላል ።

በፈረንጅኛ ፡ ደግሞ ፡ "nihilism" ፡ የሚሉት ፡ ኀሊኛ ፡ ወይም ፡ "ideology" ፡ አለ ፤ "የሀገርን ፡ ተቋማት ፡ ማፍረሻ ፣ መናኛ ፡ ዘዴ" ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። በሌላው ፡ ዓለም ፡ በገቢር ፡ ተፈጽሞ ፡ ታይቷል ፤ እንደ ፡ ዩጎስላቭያ ፡ ያሉ ፡ ጥቂት ፡ ሀገሮችም ፡ በርሱ ፡ ጠፍተዋል ። ካ 19 ኛው ፡ ምእትያ ፡ አጋማሽ ፡ እስከ ፡ 20 ኛው ፡ ምእትያ ፡ መባቻ ፥ በነኰርኳር ፡ ወይም ፡ በ"revolution" ፡ ስም ፥ በመስኮብ ፡ ምልክ ፡ ውስጥ ፡ የተነሣው ፡ የፍርሰት ፡ አዙሪት ፡ የንጉልዮሽ ፡ ወይም ፡ የ"ኒኂሊዝም" ፡ አንዱና ፡ ዐይነተኛው ፡ መዘዝ ፡ ተብሎ ፡ በታሪክ ፡ ተመዝግቧል ። "ኒኂሊዝም" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ራሱ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ዐዲስ ፡ ኹኔታ ፡ ለመግለጽ ፡ የዋለው ፡ በመስኮብ ፡ ምሁራን ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ዛሬ ፥ እንዳሰላለፋችን ፥ "አገር-አፍቃሪ" ፣ "ወግ-አጥባቂ" ፥ አለዚያም ፡ "አዘብጣጭ" ፣ "ኋላ-ቀር" ፡ ብለን ፡ ሚናቸውን ፡ የምንለየው ፡ የዚያ ፡ ዘመን ፡ የመስኮብ ፡ ምሁራን ፥ የገጠማቸውን ፡ ዐዲስ ፡ ችግር ፡ መርምረው ፥ ሲያገኙት ፡ ምክንያቱን ፡ የገለጹበት ፡ ዐዲስ ፡ ቃል ፡ ነበር ።

የመስኮብ ፡ አገር-አፍቃሪዎች ፥ የመጣባቸውን ፡ አደጋ ፡ ለይተው ፡ ስም ፡ ሲሰጡት ፥ መነሻውን ፡ ምዕራብ ፡ አውሮፓ ፥ በተለይም ፡ የጀርመን ፡ ፍልስፍና ፥ ልዩ ፡ ስሙን ፡ "ሄጌሊያኒዝም / hegelianism" ፡ ብለው ፡ ከጌኦርግ ፡ ሄገል [2] ፡ (1762-1823 ፡ ዓ.ም.) ፡ ፍልስፍና ፡ አመንጭተውታል ።

ከቶ ፡ የ"ሄጌሊያኒዝም" ፡ ወይም ፡ የሄጌልዮሽ ፥ ከርሱም ፡ የመነጩት ፡ የ"አናርኪዝም" ፡ ወይም ፡ የመረንዮሽ ፣ የ"ኒኂሊዝም" ፡ ወይም ፡ የንጉልዮሽ ፣ የ"ኮምዩኒዝም" ፡ ወይም ፡ የጋርዮሽ ፡ እና ፡ የመሳሰሉት ፡ እንደ ፡ "ናዚዝም"ና ፡ "ፋሺዝም" ፡ ያሉ ፡ ጽንፍዮሾች ፡ ("extremisms") ፥ መነሻቸውና ፡ መድረሻቸው ፡ ምን ፡ ይኾን ፧

ብዙ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ሳንገባ ፥ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ብቻ ፡ በጥቂት ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ጠቅልሎ ፡ ለመንገር ፡ ያኽል ፥ የ"ሄጌሊያኒዝም" ፡—

- መነሻው ፡ የሰው ፡ መምለክ ፡ (አምላክን ፡ በሰው ፡ መተካት) ፤
- መድረሻው ፡ ደግሞ ፥ ከሰውም ፡ ይልቅ ፡ የራስ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ መምለክ ፤

የሚሉት ፡ ራስን ፡ ማብለጥ ፥ ራስን ፡ ማስቀደም ፥ አለዚያም ፡ ራስን ፡ ማምለክ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ።

ሰው ፡ በመምለኩ ፥ ከሰው ፡ ኅሊና ፡ ውጪ ፡ እውነት ፡ (እውንነት) ፡ አይኖርምና ፥ ሰውን ፡ አንድያው ፡ የታሪክ ፡ ምስክርና ፡ የመጪው ፡ ጊዜ ፡ ተንባይ ፡ ነቢይ ፥ ከታሪክ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚረማመድ ፡ የመሻሻል ፡ መሪ ፣ ፊታውራሪ ፡ ያደርገዋል ። በዚህም ፡ አያበቃ ፤ መላኪው ፡ ሰው ፥ በታሪክ ፡ ግሥጋሤው ፥ በነጮች ፥ ከነጮችም ፡ በፕሮቴስታንት ፡ ነጮች ፡ ቊንጮነት ፥ መደዴ ፡ ዕርገቱን ፡ ከዕርከን ፡ ወደ ፡ ዕርከን ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ የሚሰፍንና ፥ ኹሉን ፡ ከልዕልናው ፡ የሚቃኝ ፡ አድርጎ ፡ ያበጃጀዋል ። ይህ ፡ ከምኞት ፡ የመነጨ ፡ ግብዝ ፡ ጥበብ ፥ ለኹለት ፡ የግራና ፡ የቀኝ ፡ ጽንፍዮሾች ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ለጋርዮሽ ፥ በሌላው ፡ ወገን ፡ ለናዚዝምና ፡ ለፋሺዝም ፡ እኩል ፡ መጋለቢያ ፡ ሜዳቸውን ፡ ሰጣቸው ። ጋርዮሽ ፡ በ"ዲያሌክቲክስ" ፡ መቂናጥ ፡ የሚፈልገውን ፡ የታሪክ ፡ ግሥጋሤ ፡ የሚሸምንበትን ፡ ስልት ፡ ሲጨብጥበት ፤ ናዚዝምና ፡ ፋሺዝም ፡ ደግሞ ፥ የነጭን ፡ "ልዕለ ፡ ሰብእና" ፡ የሚያሳምኑበትን ፡ የስብከት ፡ ጭብጥና ፡ የግፍ ፡ መሰወሪያ ፡ አገኙበት ። ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ ለምኞቶቻቸው ፡ ልጓም ፡ ሳይኖርባቸው ፥ የሌላውን ፡ መብት ፡ "በሚገባ" ፡ እየረመረሙ ፥ "በታሪክና ፡ በመብት ፡ ተመድበልናል" ፡ ባሉት ፡ የ"መሻሻል" ፡ ኺደት ፡ ውስጥ ፥ የልዕልናውን ፡ ዕርከን ፡ ተሠየሙበት ።

ይህም ፡ ሊታመን ፥ ከሄጌልዮሽ ፡ ዕርሾ ፡ የፈላው ፡ "መረንዮሽ" ፣ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ "ጋርዮሽ" ፡ በ"ቦልሼቪኮች" ፡ እና ፡ በ"ሜንሼቪኮች" ፡ አካልነትና ፡ ግዘፍ ፡ የሚረማመድ ፡ አፍራሽ ፣ ናጅ ፡ ኀይል ፡ ኾኖ ፥ ያን ፡ ታላቅ ፡ የመስኮብ ፡ ምልክ ፡ እንዳልነበረ ፡ አደረገው ። ለሰባ ፡ ዓመት ፡ በሶቪየት ፡ ኅብረት ፡ ይዘት ፡ ታጅሎ ፡ ቈይቶ ፥ መጨረሻውን ፡ በ 1981 ፡ ዓ.ም. ፥ ፍንዳታን ፡ በሚመስል ፡ መበታተን ፥ ለ 20 ፡ ለ 30 ፡ ንኡሳን ፡ ሀገሮች ፡ ተበታተነ ። "በምን ፡ ታጀለ ፧ " ፡ ቢሉ ፥ መልሱ ፡— ሥልጣኔንና ፡ ሥልጣንን ፣ ሃይማኖትንና ፡ ባህልን ፣ ሥርዐትንና ፡ ደንብን ፣ ታሪክንና ፡ ትውፊትን ፡ "ባዶ ፣ ንጉል" ፡ ብሎ ፡ በካደ ፡ የንጉልዮሽ ፡ ፍልስፍናና ፥ ኋላ ፡ ደግሞ ፡ ነባሩን ፣ ትውፊታዊውን ፡ ሥርዐት ፡ "ጠራርጎ ፡ በጣለ" ፡ በሶቪየት ፡ ኅብረት ፡ የጋርዮሽ ፡ ይዘት ።

ወደራሳችን ፡ ጒዳይ ፡ ስንመለስ ፥ ከዘመኑና ፡ ከየብሱ ፡ መራራቅ ፡ በቀር ፥ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያን ፥ ዛሬ ፡ የገጠማት ፡ አደጋ ፡ ይኸው ፡ ንጉልዮሽ ፡ ያመጣብን ፡ አደጋ ፡

2 Georg ፡ Hegel ፥ 1770-1831 ፡ A.D.


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

መኾኑ ፡ በብዙ ፡ ማስረጃዎች ፡ ይረጋገጣል ። የንጉልዮሽ ፡ አደጋው ፡ ከውስጥ ፡ ከመጣ ፡ ቅራኔ ፡ ወይም ፡ ጥያቄ ፡ ከመመንጨትም ፡ የባሰ ፥ ከውጭ ፡ በታቀደ ፣ በተመራና ፡ በተደገፈ ፥ ኢትዮጵያን ፡ የማፈራረስና ፡ አፍሪቃን ፡ የመቀራመት ፡ የምልክዮሽ ፡ (ወይም ፡ የ"*imperialism*") ፡ ዘመቻ ፡ ስልት ፡ መኾኑ ፡ ዐይነቱን ፡ ይለየዋል ፤ አደጋውንም ፡ ያቀለዋል ።

አሮጌ ፡ ሥርዐት ፥ እንደ ፡ አሮጌ ፡ ጫካ ፡ ኹሉ ፥ የጥፋት ፡ እሳት ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ እየተነሣበት ፥ ለብልቦ ፡ የሚምረውን ፡ ያኽል ፥ አቃጥሎም ፡ ያጠፋዋል ። ኢትዮጵያችን ፡ ጥንታዊት ፡ ሀገር ፡ እንደ ፡ መኾኗ ፡ መጠን ፥ በታሪኳ ፡ ዐያሌ ፡ ለውጦችንና ፡ ነውጦችን ፡ አሳልፋለች ። ምናልባትም ፥ በረዥም ፡ ዕድሜዋ ፡ "ግሎባሊዜሽን"ን ፡ ካንዴም ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሳታስተናግድ ፡ አልቀረችም ። "የብርሃን ፡ ዘመን" [3] ፡ የተባለው ፡ የፍልስፍናና ፡ የዕውቀት ፣ የጥበብና ፡ የኪነት ፡ ምርት ፡ ከረሸተበት ፡ ካ 16 ኛው ፡ ምእትያ ፡ አንሥቶ ፡ ባውሮፓ ፡ ታላቅና ፡ አጠቃላይ ፡ ለውጥ ፡ ታይቷል ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ አላቋረጠ ። ለውጡም ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ ተስፋፍቶ ፥ ያገኛቸውን ፡ ግዛታውያንም ፡ ሃይማኖታውያንም ፡ ልማዳውያንም ፡ ሥርዐቶች ፡ ይፈትናል ። የተቋቋሙትን ፡ እያደሰ ፥ ያልተቋቋሙትን ፡ እየደመሰሰ ፥ ዛሬ ፡ በየጕዳዩ ፡ የምናየውን ፡ የመንግሥታትን ፡ አህጉራዊ ፡ ሚዛንና ፡ አሰላለፍ ፡ ሰጥቶናል ። ዐያሌ ፡ ያፍሪቃና ፡ የእስያ ፣ ያውሮፓና ፡ ያሜሪካ ፥ እንዲሁም ፡ የያቅያንያ ፡ መንግሥታትና ፡ ሕዝቦች ፥ የጠፉት ፡ ጠፍተው ፥ የተረፉት ፡ ደግሞ ፡ በጠባያቸው ፡ ተለውጠው ፡ ይገኛሉ ። ኢትዮጵያም ፡ በዚሁ ፡ ፈተና ፡ ከባድ ፡ ዋጋን ፡ እየከፈለች ፡ ዐልፋ ፥ ተለዋውጣ ፥ ኹላችንም ፡ በምናውቀውና ፡ በሚያሳስበን ፡ ኹኔታ ፡ ውስጥ ፡ ትገኛለች ። የብርሃን ፡ ዘመኑ ፡ ያመጣው ፡ የርትዕ ፡ አስተሳሰብ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዐዲሷ ፡ አይደለምና ፥ ጸናችበት ፡ እንጂ ፡ አልፈረሰችበትም ፤ ተረታችለት ፡ እንጂ ፥ አልተረታችበትም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፡ "ሥልጡንሕዝብና" ፥ በመሠረቱ ፥ የርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፥ በሀገራዊ ፡ ሥርዐቷ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ የሚከበርባት ፥ ሰው ፡ በሰውነቱ ፡ የሚታይባትና ፥ በሕግ ፡ ፊት ፡ ኹሉም ፡ የተስተካከለባት ፤ ከራሷም ፡ ዐልፋ ፥ የተጠቁ ፡ ኹሉ ፡ ከቅርብም ፡ ከሩቅ ፡ ሀገር ፡ መጥተው ፡ የሚጠጉባትና ፡ የሚተርፉባት ፡ እውነተኛ ፡ "ሀገር" ፡ መኾኗ ፡ ተመስክሮላታል ። ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ተሰደው ፡ በሰላም ፡ የሰፈሩባት ፤ የክርስትና ፡ አባቶች ፡ ከሮም ፡ ምልካዊ ፡ ጥቃትና ፡ ብደላ ፡ ሸሽተው ፡ የተረፉባት ፤ የእስልምናው ፡ ነቢይ ፡ የሙሐመድ ፡ ወገኖች ፡ ከሀገራቸው ፡ ተሳደው ፡ የተጠጉባትና ፥ ሃይማኖታቸውን ፡ በሰላም ፡ ያስፋፉባት ፡ ብፅዕት ፡ ሀገር ፡ ናት ።

ዐልፎ ፡ ዐልፎም ፥ ከሀገራዊው ፡ የርትዕ ፡ ሥርዐት ፡ ውጪ ፥ ዐምባ ፡ ገነኖች ፡ የወነበዱበትንም ፥ በዘረፉና ፡ በሸፍትነት ፡ የሚተዳደሩ ፥ የሀገራዊነትን ፡ ጣዕም ፡ ገና ፡ ያልቀመሱ ፡ ጎሳዎችም ፡ የዘረፉበትንና ፡ የመዘበሩበትን ፡ ቀውጢ ፡ ዘመንም ፡ ያስተናገደች ፡ ሀገር ፡ ናት ። በድምሩ ፡ ግን ፥ ኢትዮጵያ ፡ መመዘን ፡ ያለባት ፡ በቋሚ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐቷ ፡ እንጂ ፥ በእየዘመኑ ፡ በደረሱ ፡ የውንብድና ፡ ወቅቶች ፡ ሊኾን ፡ አይገባም ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ርቱዕነት ፡ በተለይ ፡ በቅኚ ፡ ግዛት ፡ ተደጋጋሚ ፡ ወረራዎች ፡ ላይ ፡ ባሳየው ፡ የበላይነት ፡ ተረጋግጧል ።

ታዲያ ፡ ዛሬ ፡ ምን ፡ አገኘን ፧ ምን ፡ ነካን ፧

ትውልዱ ፡ ምንን ፡ ተመግቦ ፣ እንዴትስ ፡ ተኰትኵቶ ፡ አደገ ፧ ማንን ፡ አክብሮ ፥ ማንንስ ፡ ንቆ ፧ ከቶ ፡ ይህን ፡ የወሰነብንስ ፣ ያስፈጸመብንስ ፡ ማን ፡ ይኾን ፧ በየትኛውስ ፡ አገባብ ፧ መቼ ፧ ለምን ፧ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ባእምሯችን ፡ ዘወትር ፡ ይጕላላሉ ። በየምክንያቱም ፡ ወይ ፡ ላንዱ ፡ ወይ ፡ ለሌላው ፡ ጥያቄ ፡ መልሱን ፡ እያገኘን ፥ "*ለኹሉሳ ፧* " ፡ ስንል ፡ ደግሞ ፥ በጠቅላላው ፥ አኹንም ፡ መልሱ ፡ ንጉልዮሽ ፡ ኾኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ንጉልዮሽ ፥ ባጋጣሚ ፡ አልወደቀብንም ፤ ምናልባት ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ እየወለደ ፡ በተከታተሉ ፡ አራት ፡ ረድፎች ፡ ተረማምዶብናል ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። ለእያንዳንዱ ፡ ረድፍ ፡ ማስረጃውን ፡ እዚህ ፡ ማቅረቡ ፡ "*ለቀባሪው ፡ አረዱት*" ፡ ስለሚኾን ፥ ለየረድፉ ፡ ከዋና ፡ ዋና ፡ ደረጃዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹን ፡ በክፍል ፡ 2 ፡ እዘረዝርና ፥ በተለይ ፡ በምንገኝበት ፡ ባራተኛው ፡ ወሳኝ ፡ ረድፍ ፡ አኹን ፡ የሚታየውን ፡ አደጋና ፡ ሊከተል ፡ የታቀደውን ፡ ጥፋት ፡ አመልክቼ ፥ ለጥፋቱ ፡ ማብረሻዎቹ ፡ ይኾኑ ፡ የመሰሉኝን ፡ ሀገራውያን ፡ ሥራዎች ፡ በክፍል ፡ 3 ፡ ባጪሩ ፡ በመጠቄም ፡ አጠቃልላለኹ ።

- የመዠመሪያው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1901 ፡ ዓ.ም ፡ እስከ ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ዘመን ፤
- ኹለተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፥ የስእነት ፡ ዘመን ፤
- ሦስተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከየካቲት ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ የውንብድና ፡ ዘመን ፤
- አራተኛውና ፡ የመጨረሻው ፡ ረድፍ ፥ ከግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፥ የ"*ዩጎዝላቪዜሽን*" ፡ ዘመን ።

(*ይቀጥላል ።* )

3 Age of Enlightenment | age de lumière.

# ክዋኔ
# CONSTITUTION

*[በዚህ ፡ ዐምድ ፥ ስለሕገ ፡ መንግሥት ፡ (ወይም ፡ ክዋኔ) ፡ ጉዳይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ ይቀርቡበታል ። ]*

## *የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ግሶችን ፡ ስለማዘጋጀት ።*

---

ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ክዋኔ ፡ ዐዲስ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። በቀደመው ፡ ጽሑፋችን ፡ እንዳየነው ፥ ቢያንስ ፡ ለ 749 ፡ ዓመት ፡ የጽሑፍ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ባለቤት ፡ ኾና ፥ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ሲያድር ፣ ሲተዳደር ፡ የኖረ ፡ ሐራ ፡ ሕዝብ ፡ መኾኑ ፥ ሀገሩም ፡ ሐራ ፡ ሀገር ፡ መኾኗ ፡ ተመስክሯል ። ኾኖም ፥ "እሳት ፡ ለፈጀው ፡ ምን ፡ ይብጀው ፨ " ፡ እንዲሉ ፥ ኢትዮጵያ ፡ ባለፉት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፥ ባህሏን ፣ ታሪኳን ፣ ቋንቋዋን ፡ ያመሰቃቀሉ ፡ ነውጦች ፡ ተደራርበውባት ፥ ዛሬ ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾና ፥ ተደማምጦና ፡ ተግባብቶ ፡ ለመምከርና ፡ ለመወሰን ፡ በሚያስችል ፡ አቋም ፡ ሕዝቧ ፡ አይገኝም ። ይህን ፡ ችግራችንን ፡ ባጪር ፡ ጊዜ ፡ ለመፍታት ፥ የኾላችን ፡ የጋራ ፡ ጥረት ፡ ይፈለጋል ።

ኢትዮጵያ ፡ የርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንደ ፡ መኾኗ ፡ መጠን ፥ በሀገራዊ ፡ ባህላችንም ፡ ኾነ ፡ በኅብረተሰብ ፡ ባህላችን ፥ እጅግ ፡ የዳበረ ፡ የጉባኤና ፡ የሸንጎ ፡ ሥርዐት ፡ አለን ። ትኽክለኛ ፡ የሽግግር ፡ መንግሥት ፡ ሲቋቋም ፥ የመዠመሪያው ፡ ሥራ ፡ ይህን ፡ ባህላዊ ፡ መጥሪታችንን ፡ ወዲያው ፡ በሥራ ፡ ማዋል ፡ ይኾናል ። ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መረቀቅና ፡ መጽደቅ ፡ አለበት ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጠይቋል ፥ ኹኔታውም ፡ አስገድዷል ። መሳው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሚመርጣቸው ፡ እንደራሴዎቹ ፡ አማካይነት ፡ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አርቅቆና ፡ አጽድቆ ፡ ቋሚ ፡ መንግሥቱን ፡ ሊመሠርትበት ፡ ይሻል ። አኹን ፡ በምንገኝበት ፡ ኹኔታ ፥ ነባሮቹ ፡ የስያሳ ፡ ቃሎች ፡ ወይም ፡ ግሶች ፡ ተረስተዋል ፥ ወይ ፡ አላግባብ ፡ ተነውረው ፡ ካገልግሎት ፡ ውጭ ፡ ኾነዋል ፥ ወይ ፡ ትውልዱ ፡ በባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ ተምሮ ፡ ሀገራዊ ፡ ቋንቋው ፡ ዐማርኛ ፡ ቸግሮታል ፥ ወይ ፡ የባሰውን ፥ ኾነ ፡ ተብሎ ፡ በዘመቻ ፡ መልክ ፡ በተካኼደ ፡ የቋንቋ ፡ መዘበራረቅ ፥ ርስ ፡ በርስ ፡ መግባባቱ ፡ አቅቶናል ።

አጠቃላይ ፡ ችግሩን ፡ ለመፍታት ፥ ከሥር ፡ ከመሠረቱ ፡ መነሣቱ ፡ ይጠቅማልና ፥ በስያሳ ፡ ግሶች ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ ዝብርቅርቅ ፡ አስቀድሞ ፡ መወገድ ፡ ይኖርበታል ።

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የስያሳ ፡ ግሶችን ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ ለሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ለክዋኔ ፡ ሥራ ፡ የሚውሉትን ፥ በትኽክል ፡ ለመደንገግ ፡ በቅድሚያ ፡ መሟላት ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ለማስገንዘብ ፡ ይሞክራል ።

ትውፊታዊውን ፡ የስያሳ ፡ ግስ ፡ ከወደቀበት ፡ በማንሣትና ፡ ጥልቅ ፡ ፍልስፍናውን ፡ በማስታወስ ፥ ማዘመን ፡ የሚያስፈልገውንም ፡ ባግባቡ ፡ በማዘመን ፥ ወደተፈለገለት ፡ አገልግሎት ፡ እንዴት ፡ እንደሚውል ፡ በጥቂቱ ፡ ያሳያል ።

በመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ ስለስያሳ ፡ ግስ ፡ ርባታ ፡ ባጪሩ ፡ እናብራራለን ።

በኹለተኛውና ፡ የመጨረሻ ፡ ክፍል ፥ በዋና ፡ ዋና ፡ የክዋኔ ፡ ግሶች ፡ ላይ ፡ በዘመናችን ፡ የሚታዩትን ፡ የትርጉም ፡ መፋለሶች ፡ በጥቂቱ ፡ ገልጠን ፥ እንዴት ፡ ሊታረሙ ፡ እንደሚችሉ ፡ ባጪሩ ፡ እናመለክታለን ።

### 1 ፤ ስለስያሳ ፡ ግስ ፡ ርባታ ።

እንደሚታወቀው ፥ ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፡ የዳበረ ፡ የመርባት ፡ ጠባይ ፡ አላቸው ። በስያስኛም ፡ ኾነ ፡ በማንኛው ፡ የጥናት ፡ መስክ ፡ የምንሠራባቸው ፡ ቃላት ፡ ከመሠረታዊው ፡ ዘር ፡ በግስ ፡ ወይም ፡ በገስሳ ፡ ይገኛሉ ። ምንም ፡ በየጥናት ፡ መስኩ ፡ በብዙ ፡ ሺሕ ፡ የሚቈጠር ፡ የግስ ፡ መጠን ፡ ቢኖር ፥ እነዚህ ፡ ግን ፡ የሚገሰሱት ፡ ምናልባት ፡ 10 ፡ ጊዜ ፡ ካነሰ ፡ የዘር ፡ መጠን ፡ ይኾናል ።

ለምሳሌ ፥ ዋናው ፡ ጉዳያችን ፡ የኾነው ፡ "ክዋኔ" ፡ ብለን ፡ የምንጠራው ፡ አካል ፡ ብዙ ፡ ተያያዥ ፡ ዕስባቶች ፡ አሉት ። ዘሩ ፡ በግእዝ ፡ "ከወነ" ፡ ነው ፤ ይህም ፡ "ኾነ ፣ ተፈጠረ ፣ ቆመ" ፡ ማለት ፡ ነው [4] ፤ "መንግሥት ፡ ማቆም ፡ እንዲሉ" ።

በርባታ ፡ ዝርዝሩ ፡ በከፊል ፡ ያየነው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ካ 10 ፡ ያላነሱ ፡ ሌሎች ፡ ግሶችን ፡ ይሰጠናል ፡—

| | ግእዝ | ዐማርኛ | እንግሊዝኛ | ፈረንሳይኛ |
|---|---|---|---|---|
| አርእስት | ከዊን/ከዊኖት | መኾን | to be | Être, v. |
| ቀዳማይ | ኮነ | ኾነ | is | est |
| ሣልስ ፡ ቅጽል | ከዋኒ | ኺኝ | Being, n. | Être, n. |

---

4 አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ "ከዊን"ን ፡ እንደሚከተለው ፡ ይፈቱታል ፡— *"መኾን ፥ መባል ፤ ሳይለወጡ ፥ በሱታፌና ፡ በምሳሌ ፣ በግብር ፡ ሌላ ፡ ስምን ፡ መቀበል ። ወይም ፡ በጭራሽ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ባሕርይ ፡ መለወጥ ፥ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ መኾን ፤ ተለውጦና ፡ ተገልብጦ ፡ በሌላ ፡ ባሕርይ ፡ ስም ፡ መጠራት ፥ ያው ፡ ግን ፡ ጨገሬታውና ፡ ምልክቱ ፣ አሠሩ ፣ ቢጋሩ ፣ ህላዌው ፡ ሳይጠፋ ። "* **ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ** ፡ (አለቃ) ፤ ***መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ*** ፤ አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ 1948 ፡ ዓ.ም. ፤ ገጽ ፡ 524 ። በተመሳሳይ ፥ መላከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ጀምበሬ ፡ "ኩነት"ን ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ይፈታሉ ፡— *"ኩነት ፥ ተከፍሎ ፣ ተፈልጦ ፡ ሳይኖርበት ፥ በተዋሕዶ ፣ በተጋብኦ ፣ ባንድነት ፥ አካላትን ፡ በህልውና ፡ ያገናዘበ ፥ ባንድ ፡ መለኮት ፡ ያለ ፣ የነበረ ፣ የሚኖር ፡ ነው ። "* **አድማሱ ፡ ጀንበሬ** ፡ (መልአከ ፡ ብርሃን) ፤ ***ኰሾሐ ፡ ሃይማኖት*** ፤ ትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፥ 1989 ፡ ዓ.ም. ፤ ገጽ ፡ 120)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሳድስ ፡ ቅጽል | ክውን | ክውን/ኹን | constituted | constitué |
| መስም ፡ ቅጽል | መክውን | ክዋኘ | constituent | constituant |
| | | | constituency | Circonscription électorale |
| ሳቢ. ፡ ዘር | ኩነት | ኩነት/ኹነት | State | État |
| ሳቢ. ፡ ዘር ፡ (2) | ክዋኔ | ክዋኔ | Constitution | Constitution |
| ባዕድ ፡ ዘር | ምክዋን | መከወኛ / መኾኛ | State system | système étatique |
| ጥሬ ፡ ዘር | | ክወና | | |

እንደሚታወቀው ፥ ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፡ ከ 9 ፡ እስካ 15 ፡ የሚደርሱ ፡ የግስ ፡ አዕማድ ፡ አሏቸው ፦ ደራጊ ፣ አድራጊ ፣ ተደራጊ ፣ አስደራጊ ፣ አደራራጊ ፣ ተደራራጊ ፣ ወዘተ. ፡፡ በሰንጠረዡ ፡ ላይ ፡ በደራጊ ፡ ወይም ፡ አድራጊ ፡ ዐምድ ፡ የሚገኙትን ፡ ግሶች ፡ በከፊል ፡ አይተናል ፡፡ ባስደራጊ ፣ በተደራጊ ፣ ባደራራጊ ፣ በተደራራጊ ፣ ወዘተ. ፡ ዐምዶች ፡ እንደ ፦

| | | | |
|---|---|---|---|
| አኾነ | ተኾነ | አኳኳነ | ተኳኳነ ... |
| አኳኘ | ተኳኘ | አኳኳኘ | ተኳኳኘ ... |
| ማኾኛ | መኾኛ | ማኳኳኛ | መኳኳኛ... |

ያሉ ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ ግሶች ፡ አሉ ፡፡

ምዕራባውያን ፡ ቋንቋዎች ፡ ካድራጊና ፡ ከተደራጊ ፡ አዕማድ ፡ የሚያልፍ ፡ የግስ ፡ ርባታ ፡ ስለሌላቸው ፥ በምዕራባውያን ፡ ቋንቋዎች ፡ ባንድ ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ እንጂ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ የማይነገሯቸውን ፡ አደራራጊና ፡ ተደራራጊ ፡ ... ፡ ኹኔታዎችን ፥ ግእዝ-ዐማርኛ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ስለሚያናግረን ፥ ይህ ፡ ለሥነ ፡ ግዛትም ፡ ኾነ ፡ ለማንኛውም ፡ የጥናት ፡ መስክ ፡ ተጨማሪ ፡ የሐሳብ ፡ ኀይልን ፡ ይሰጠናል ፡፡ ዛሬ ፡ ሙሉ ፡ ለሙሉ ፡ ሠርተንበት ፥ ሀገርንና ፡ የሰው ፡ ልጅን ፡ በጠቅላላው ፡ ልንጠቅምበት ፡ ይገባል ፡፡

ርእሱ ፡ እጅግ ፡ ሰፊና ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፤ እስካኹን ፡ የገለጽነው ፡ ሐሳብ ፡ ያልተገነዘቡትን ፡ ለማስገንዘብ ፣ የተዘነጉትን ፡ ለማስታወስ ፡ እንጂ ፥ ሙሉ ፡ ዝርዝሩ ፡ ይጻፍ ፡ ቢባል ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ መድበል ፡ አይመልሰውም ፡፡

## 2 ፤ ስለትርጒም ፡ መፋለስና ፡ ተመልሶ ፡ መቃናት ፡፡

በክዋኔ ፡ ግስ ፡ ረገድ ፥ አራት ፡ ዐይነት ፡ ኹኔታዎች ፡ ይገጥሙናል ፤

- ቃሉ ፡ ለሐሳቡ ፡ የተስማማ ፤
- ቃሉ ፡ ከሐሳቡ ፡ ያልተስማማ ፤
- ቃሉ ፡ ለሐሳቡ ፡ ያልተገኘ ፤
- ቃሉ ፡ ለሐሳቡ ፡ ያረጀና ፡ የሚታደስ ፤
- ብዙ ፡ ማማረጫዎች ፡ ቃሎች ፡ ለሐሳቡ ፡ ሲኖሩ ፡፡

### 2.1 ፤ ቃሉ ፡ ለሐሳቡ ፡ የተስማማ ፡፡

ለምሳሌ ፡ "ሕግ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ለሐሳቡ ፡ ትኽክለኛ ፡ ፍቺ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ እንዳለ ፡ እንቀበለዋለን ፡፡ ቃሉ ፡ **አምሳያ** ፡ ቢኖረው ፥ እንዳስፈላጊነቱ ፡ ባምሳያው ፡ ልንሠራ ፡ እንችላለን ፡፡ ለምሳሌ ፥ ባንዳንድ ፡ ኹኔታ ፥ በ"ሕግ" ፡ ፈንታ ፡ "ደንብ" ፡ ወይም ፡ "ሥርዐት" ፡ ማለት ፡ ይቻላል ፡፡

### 2.2 ፤ ቃሉ ፡ ከሐሳቡ ፡ ያልተስማማ ፡፡

ይህ ፡ ከትርጒም ፡ መፋለስ ፡ የሚነሣ ፡ ኹኔታ ፡ በዘመናችን ፡ ዘወትር ፡ ይገጥመናል ፡፡ ለምሳሌ ፦

- "ብሔር" ፡ ምድር ፡ ወይም ፡ ስፋት ፡ ማለት ፡ ሳለ ፥ በስሕተት ፡ ጎሳ ፡ ለማለት ፡ ውሏል ፤ "ውልደት" ፡ ተብሎ ፡ ሊስተካከል ፡ ይችላል ፡፡
- እንዲሁም ፥ "እግዚእና" ፡ ወይም ፡ "ገዢነት" ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ "ልዕልና" ፡ ወይም ፡ "ሉዓላዊነት" ፡ ሲሉ ፡ ይሰማል ፤ ይህም ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡፡

### 2.3 ፤ ቃሉ ፡ ለሐሳቡ ፡ ያልተገኘ ፡፡

በሕግ ፡ ረገድ ፡ በትውፊታዊ ፡ ሥርዐታችን ፡ ያልነበሩ ፡ ዐዳዲስ ፡ ቃላትን ፡ ሳንተረጒም ፡ በውጭ ፡ ቋንቋ ፡ ቃልነታቸው ፡ ይዘናቸዋል ፡፡ ለምሳሌ ፡ "ፌዴራል" ፡ እንላለን ፡፡ ለእንደዚህ ፡ ያሉቱም ፡ ትኽክለኛውን ፡ ትርጒማቸውን ፡ እንሰጣቸዋለን ፡፡ "ፌዴራል"ን ፡ ሲቃወንት ፡ **"ደባል"** ፡ ብለው ፡ ተርጒመውታል ፡፡ ገና ፡ ያልተተረጐሙ ፡ በሺሕ ፡ የሚቈጠሩ ፡ የውጭ ፡ ቃላት ፡ አሉ ፡፡ ከነዚህ ፡ አንዱ ፡ "ፖሊስ" ፡ ነው ፡፡

### 2.4 ፤ ቃሉ ፡ ለሐሳቡ ፡ ያረጀና ፡ የሚታደስ ፡፡

ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ገባ ፥ በጸጥታ ፡ ረገድ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ የጠበቀ ፡ ግንኙነት ፡ ነበረውና ፥ ጠቅላላ ፡ የጸጥታውን ፡ መዋቅር ፡ እንዲያቋቁሙለት ፡ ሰጥቷቸው ፡ ነበር ፡፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፥ የፖሊስ ፡ መኰንኖችን ፡ ማዕርግ ፥ ከነበረበት ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አጠራሩ ፡ ለውጦ ፥ ቃል ፡ በቃል ፡ የእንግሊዝኛ ፡ አጠራርን ፡ ላከከበት ፡፡ ነባሩ ፡ የማዕርግ ፡ አሰያየም ፥ እንደ ፡ ወታደራዊው ፡ አሰያየም ፥ ከምክትል ፡ ፲ ፡ አለቃ ፥ ፶ ፡ አለቃ ፣ ... ፣ ፻ ፡ አለቃ ፣ ሻምበል ፣ ሻለቃ ፡ እያለ ፡ የሚኼደውን ፥ "ሳጅን" ፣ "ኮንስታብል" ፣ "ኢንስፔክተር" ፣ "ኮማንደር" ፡ ... ፡ ማለቱ ፡ ሕዝብን ፡ ከማደናገር ፡ ሌላ ፡ አንዳች ፡ ያመጣው ፡ ጥቅም ፡ የለም ፡፡ ለምሳሌ ፡ "ኮንስታብል" ፥ ወይም ፡ "constable" ፥ ቃል ፡ በቃል ፥ "የበረት ፡ አለቃ" ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ለዘመኑ ፡ እንግሊዝኛም ፡ እንኳ ፡ ያረጀ ፣ ያፈጀ ፡ ቃል ፡ በመኾኑ ፥ ዐማርኛን ፡ የ"ጃንክ" ፡ ማራገፊያ ፡ ማድረጉ ፡ አይገባም ፡፡ ሌሎቹም ፡ እንደዚሁ ፡ ጊዜው ፡ ያለፈባቸው ፡ ትርጒም-የለሽ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ፤ ሊወገዱ ፡ ይገባል ፡፡ የማዕርጉ ፡ ስም ፡ የሥራውን ፡ ጠባይና ፡ ተዋረድ ፡ በግእዝ ፡ ወይ ፡ ባማርኛ ፡ መግለጽ ፡ ይኖርበታል ፡፡

### 2.5 ፤ ብዙ ፡ ማማረጫዎች ፡ ቃሎች ፡ ለሐሳቡ ፡ ሲኖሩ ፡፡

ለምሳሌ ፡ እላይ ፡ ላየነው ፡ "እግዚእና" ፡ ወይም ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡፡

በፈረንጅኛ ፡ (sovereignty | souveraineté) ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፥ ቢያንስ ፡ 5 ፡ ማማረጫዎች ፡ በግእዝና ፡ ባማርኛ ፡ አሉልን ፡—

*"ገዢነት"* ፤

*"ስፍነት"* ፤

*"ምስፍና"* ፤

*"መባሕት"* ፤

*"ብውሕና"* ።

የተለመደው ፡ *"እግዚእና"* ፡ ቢኾንም ፥ ለየት ፡ ላለ ፡ ኹኔታም ፡ ኾነ ፡ አገላለጥ ፡ የሚገባውን ፡ መርጠን ፡ እናውላለን ።

ለዚህ ፡ ኹሉ ፡ ሥራ ፡ እንግዲህ ፡ የጋራ ፡ ዕውቀትን ፡ መሰብሰብ ፡ አለብን ። ሊቃውንት ፡ አባቶቻችን ፡ ይህኑ ፡ ቀድመው ፡ ዐስበው ፡ ያቈዩን ፡ የግእዝም ፡ ያማርኛም ፡ መዛግብተ ፡ ቃላት ፡ አሉልን ። *"ዐውደ ፡ ቀለም"* ፡ የተባለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር[5] ፡ እነዚህንና ፡ የሌሎች ፡ ቋንቋዎችንም ፡ መዛግብተ ፡ ቃላትና ፡ ማተራጐሚያቸውን ፡ በነጻ ፡ ስላበረከተልን ፥ ሥራችን ፡ እጅጉን ፡ ቀልጥፏል ።

መደምደሚያውን ፥ እፊታችን ፡ የተደቀነውን ፡ ታላቅ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥራ ፡ በብቃት ፡ የምንወጣው ፥

- አንድም ፥ ሙሉውን ፡ ሀገራዊ ፡ ዕውቀት ፡ ስናሳትፍ ፥
- አንድም ፥ ሥራው ፡ በመላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ውክልና ፡ ሲከናወን ፡

ነውና ፥ ለዚህ ፡ በጎ ፡ ውጤት ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ ኹላችንም ፡ ተግተን ፡ እንድንተባበር ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ ጥሪያችንን ፡ በትሕትና ፡ እናስተላልፋለን ፨

# ከመቃብር ፡ በላይ ።

## "እግዜር ፡ ያጥናሽ ፤ የሚበጀውን ፡ ይላክልሽ ። "

መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ [6] ።

ሕዝብሽ ፡ እያነባ ፥ እንጀራ ፡ ተርቦ ፥
አካላዊ ፡ ኀይሉ ፡ በችጋር ፡ ተሰልቦ ፥
የምትሰጪው ፡ ዐጥተሽ ፥ የምታነጒቺለት ፥
የሚያጋድድ ፡ ታጥቶ ፥ የረባ ፡ ኀረቤት ፥
ዐይንሽ ፡ እንደ ፡ ናሴ ፡ እንደ ፡ ዋልካው ፡ መሬት ፥
በብካይ ፡ ተነድሎ ፥ ጨንቆሽ ፡ ብታነቢ ፥
ብትቅበዠበዢ ፥ ብትርገበገቢ ፥
ብትጣሪ ፡ አምርረሽ ፥ ብታረበርቢ ፥
መልካም ፡ ወዳጅ ፡ ዐጥተሽ ፥ የሚል ፡ እዚህ ፡ ግቢ ፥
ልቅሶሽም ፡ በርክቶ ፥ ሐዘንሽ ፡ ዐይሎ ፥
እየተጨናቈርሽ ፡ በዐይንሽ ፡ ጭገር ፡ በቅሎ ፥
ዋይታ ፡ በዝቶብሽ ፥ ተዘውትሮ ፡ ውሎ ።
እግዜር ፡ ያጥናሽ ፤
የሚበጀውን ፡ ይላክልሽ ።
አንጋፋ ፡ ልጆችሽ ፥ በኵሮችሽም ፡ ጠፍተው ፤
ይበልጦቹ ፡ እፊትሽ ፥ አጠገብሽ ፡ ታርደው ፤
ማሚጠጫዎቹ ፥
የኋላ ፡ ልጆችሽ ፥ ገና ፡ ማቲዎቹ ።
እያወኩ ፡ ባዝነው ፤
በውድማ ፡ ተረጭተው ፤
አረኽ ፡ ተንከራተው ፤
በዱር ፡ ተንቀዋለው ፤
ባላገር ፡ አጫርሰው ፤
ባህል ፡ አደፍርሰው ፤
እምነት ፡ አነውረው ።
በቈሎ ፡ ሲፈጩ ፤
ነድደው ፡ ሲቈላጩ ።
ውሃ ፡ ጠራርጓቸው ፥
ናዳ ፡ አውርዷቸው ፥
ድንጋይ ፡ ተጭኗቸው ፥
ወባው ፡ አንድዷቸው ፥
ችጋር ፡ ቈንድዷቸው ፥
በጥይት ፡ ተቈልተው ፥
በሹመት ፡ ተላልቀው ፥
ቀሪዎቹ ፡ አምልጠው ፥
ኹሉም ፡ ሙስሙስ ፡ ብለው ፥
መንምነው ፤ ገርጥተው ፥
ወቅዘው ፤ ሞግርረው ፥
ገቡ ፡ በሰው ፡ መንደር ፥
በማያውቁት ፡ አገር ።
ገረድ ፤ አሽከርነት ፡
ዐደሩ ፡ ሎሌነት ።
እግዜር ፡ ያጥናሽ ፤
የሚበጀውን ፡ ይላክልሽ ።
በዐምባሽ ፤ በከተማሽ ፤ በየወህኒ ፡ ቤቱ ፡
ታፍሰው ፡ የታጐሩ ፡ በየምክንያቱ ፥
እኽል ፡ ውሃ ፡ ሲሉሽ ፡ እንዲሁ ፡ የሞቱ ፤
አድኘን ፤ ታደጊን ፡ የዛሬን ፡ በብርቱ ።
ቢማጠኑሽ ፡ ጨንቆሽ ፡ ብትወናጨፊ ፥
ትኾኚውን ፡ ዐጥተሽ ፡ አብዝተሽ ፡ ብትለፊ ፥
ልቅሶሽ ፡ አድማጭ ፡ ዐጥቶ ፥ ከንቱ ፡ ኾኖ ፡ እሪታሽ ፥
ጨፍጭፈው ፤ ጨፍጭፈው ፡ በድን ፡ አስታቀፉሽ ፨

5 http://www.awdeqelem.net

6 በ 1970 ዎቹ ፡ በሱዳን ፡ በረሓ ፡ በጠላት ፡ የተገደለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የነጻነት ፡ ታጋይ ።


©ኢ.ህ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# ዜና ፡ ስሌት ።

Computing News | Nouvelles d'informatique




## ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፤ የተሟላ ፡ ያማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ማረሚያ ።

—

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ የመዠመሪያው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነጻ ፡ ባለፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያና ፡ ባለመዝገበ ፡ ቃላት ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ ነው ። የመዠመሪያ ፡ ክለሳው ፡ መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2008 ፡ ዓ.ም. ፥ ክለሳ ፡ 1.2 ፡ ደግሞ ፡ ሚያዝያ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ 2011 ፡ ወጥቷል ።

ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ቃላትን ፡ የማርባት ፣ የመዘርዘርና ፡ የማዋሐድ ፡ ጠባይ ፡ ስላለው ፥ ርሱን ፡ የሚመጥን ፡ የፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያ ፡ ለመሥራት ፡ እጅግ ፡ ያስቸግራል ። ለማስታወሻ ፡ ያኽል ፡ የሚከተለውን ፡ እንመልከት ።

በእንግሊዝኛ ፡ *"we dream the world"* ፡ ቢል ፥ ወይ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ *"nous rêvons le monde"* ፡ ቢል ፥ ወዳማርኛ ፡ ስንተረጕመው ፥ *"ዓለምን ፡ ዐለምን"* ፡ ይላል ። ነገር ፡ ግን ፥ ሳንጠነቀቅ ፥ ዐማርኛውን ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ የጻፍነው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ወይ ፡ ስሕተት ፡ ይኾናል ፥ አለዚያም ፡ ትርጕምን ፡ ይለውጣል ። ለምሳሌ ፦

*"አለምን ፡ ዐለምን"* ፡ ቢል ፥ *"ምንም ፡ ሳይኖረን ፡ ሕልምን ፡ ዐለምን"* ፡ ማለት ፡ ይኾናል ።

*"አለምን ፡ ዓለምን"* ፡ ቢል ፡ ደግሞ ፥ *"ዓለምን ፡ አስለምን"* ፡ ማለት ፡ ይኾናል ።

*"አለምን ፡ አለምን"* ፡ ቢል ፡ ደግሞ ፥ *"ምንም ፡ ምን ፡ ሳይኖር"* ፡ ማለት ፡ ይኾናል ።

*"አለምን ፨ አለምን ፨ "* ፡ ቢል ፡ ደግሞ ፥ "ብሷልምን ፨ ብሷልምን ፨ " ማለት ፡ ይኾናል ።

ወዘተ... ።

እንዲህ ፡ የተወሳሰበውን ፡ ያማርኛ ፡ አጻጻፍ ፡ ነው ፡ "ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የቃኘልን ።

ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ ቃላትን ፡ በሦስት ፡ ቋንቋዎች ፡ ባማርኛ ፣ በእንግሊዝኛና ፡ በፈረንሳይኛ ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ያተራጕማል ። ክለሳ ፡ 1.2 ፡ ደግሞ ፡ ግእዝንና ፡ ሶማልኛን ፡ በጥቂቱ ፡ ማተራጐም ፡ ዠምሯል ።

በዚያው ፡ በ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ መሳሊያ ፡ ውስጥ ፦

- ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ (የደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድና ፡ የተሰማ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል) ፤
- የግእዝ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ (የኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ) ፤
- የእንግሊዝኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ (የ WordNet ፡ አሜሪካዊ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት) ፤
- የፈረንሳይኛ ፡ ግስ ፤

ተከተውበታል ።

ያሜሪካን ፡ እንግሊዝኛ ፡ ጽሑፍንና ፡ የሶማልኛን ፡ የቁቤ ፡ ጽሑፍ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ለመመለስ ፡ የሚያስችል ፡ መመለሻም ፡ ዐብሮ ፡ ተሰጥቷል ። ይህ ፡ በተለይ ፡ ለደራስያንና ፡ ለማወራኛ ፡ ድርጅቶች ፡ እጅግ ፡ የሚረዳ ፡ አገልግሎትን ፡ ይሰጣል ።

ሙሉ ፡ መረጃውን ፡ ዐብሮት ፡ ከሚመጣው ፡ የ 107 ፡ ገጽ ፡ መመሪያ ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ።

*"ዐውደ ፡ ቀለም"* ፡ ነጻ ፡ መሳሊያ ፡ ነው ፤ ከመርበቢያው ፡ ከ awdeqelem.net ፡ በነጻ ፡ ይገኛል ። ዐብሮት ፡ *"ዋዜማ ፡ ሥርዐት"* ፡ የተባለ ፡ የመፍቻ ፡ ገበታና ፡ የቅርጸቶች ፡ ሥርዐት ፡ ይመጣልና ፥ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ወዲያውኑ ፡ የጽሑፍ ፡ አምራች ፡ ይኾንበታል ።

*"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንውም ፡ በ*"ዐውደ ፡ ቀለም"* ፡ ስለሚሠራ ፥ ጥቅሙን ፡ በገቢር ፡ አግኝቶበታል ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# ብሔረ ፡ ጥበብ ።

Universe of Science | Univers de la science

## ምድርና ፡ ኅዋ ።

### ክፍል ፡ 2 ፤ መዓልትና ፡ ሌሊት ።

ምድራችን ፡ ራሷን ፡ ወዳንድ ፡ ወገን ፡ ዘንበል ፡ አድርጋ ፡ በማይለወጥ ፡ ዝግመት ፡ ከምዕራብ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ የምትሽከረከርን ፡ እንዝርት ፡ ትመስላለች ። በራሷ ፡ ላይ ፡ እየተሽከረከረች ፥ በማይለወጥ ፡ **ምሕዋርም** ፡ (circuit) ፡ በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ ታውዳለች ።

በራሷ ፡ አንድ ፡ ዙር ፡ ለመዞር ፡ 24 ፡ ሰዓት ፡ ይፈጅባታል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፥ የፀሓይ ፡ ብርሃን ፡ ባገኘው ፡ የምድር ፡ ግጽ ፡ መዓልት ፡ ወይም ፡ ቀን ፡ ይኾናል ፤ ባላገኘውና ፡ በጨለመው ፡ ደግሞ ፡ ሌሊት ፡ ይኾናል ። በፀሓይ ፡ አንጻር ፥ እንደ ፡ ምድሪቱ ፡ ዝንባሌ ፥ የመዓልትና ፡ የሌሊት ፡ ሰዓት ፡ ካ 12 ፡ ሰዓት ፡ ዝቅ ፡ ወይም ፡ ላቅ ፡ ይላል ።

ምድር ፥ በራሷ ፡ እየተሽከረከረች ፥ በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ የምታውድበት ፡ **ዑደት** ፡ (orbit) ፡ 365 ፡ ቀን ፡ ከሩብ ፡ ይፈጅባታል ፤ ይህንም ፡ 1 ፡ ዓመት ፡ እንለዋለን ። አንዱ ፡ ዓመት ፡ ተራውን ፡ በወራት ፡ ይከፈላል ። በኢትዮጵያ ፡ የዘመን ፡ አቈጣጠር ፥ ዓመቱን ፡ ባ 12 ፡ ባለ 30 ፡ ቀናት ፡ ወራት ፡ (መስከረም ፣ ጥቅምት ፣ ኅዳር ፣ ታኅሣሥ ፣ ጥር ፣ የካቲት ፣ መጋቢት ፣ ሚያዝያ ፣ ግንቦት ፣ ሠኔ ፣ ሐምሌ ፣ ነሐሴ) ፡ እና ፡ ባ 1 ፡ ባለ 5 ፡ ወይም ፡ 6 ፡ ቀናት ፡ ወር ፡ (ጳጉሜ) ፡ እንከፍለዋለን ።

ለፀሓይ ፡ የቀረበው ፡ የምድር ፡ **ወገብጌ** ፡ (equator) ፡ የሚሞቀውን ፡ ያኽል ፥ ለፀሓይ ፡ የራቁት ፡ ሰሜናዊውና ፡ ደቡባዊው ፡ ዋልታዎች ፡ አርክቲክና ፡ አንታርክቲክ ፡ ዓመት ፡ ከዓመት ፡ ግግር ፡ በረዶን ፡ ይለብሳሉ ። ከኹለቱ ፡ መኻከል ፡ የሚገኘው ፡ ክፍል ፡ ከቀዝቃዛ ፡ እስከ ፡ ሞቃት ፡ አየርን ፡ ያስተናግዳል ። ከዚህ ፡ ጋራ ፥ እንደምድር ፡ ዝንባሌና ፡ እንደምሕዋሩ ፡ አካባቢ ፥ የአየር ፡ ንብረቱ ፡ ስለሚለውጥ ፥ እስከ ፡ አራት ፡ የሚደርሱ ፡ **ብሬቶች** ፡ (seasons | saisons) ፡ ይታያሉ ። እነዚህም ፡ መፀው ፡ (መከር) ፣ ሐጋይ ፡ (በጋ) ፣ ጸደይ ፡ (በልግ) ፣ ክረምት ፡ ይባላሉ ። ባንዳንድ ፡ አካባቢ ፡ ደግሞ ፡ ክረምትና ፡ በጋ ፡ ኾነው ፡ ለኹለት ፡ ይከፈላሉ ።

በምድር ፡ ውስጣውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ አስኳል ፡ የቀለጠ ፡ ብረት ፡ በመኾኑ ፥ የምድር ፡ መሽከርከር ፡ ብረቱን ፡ እንደ ፡ ፈልቅ ፡ ወይም ፡ ማግኔት ፡ ስለሚያደርገው ፥ በ**መርሐ ፡ ሰሜን** ፡ (compass | boussole) ፡ ለመመራት ፡ ይፈቅዳል ❖

# ከታሪክ ፡ አንድ ፡ ዐምድ ።

History Column | colonne d'histoire

## "ሐፄጌ ። "

ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ (1862-1936 ፡ ዓ.ም.) ።

(ከ"*መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ ።* " ፡ ገጽ ፡ 457 ፡ የተቀዳ ። )

http://www.gzamargna.net/html/gzMezgebeQalat457.html

**ሐፄጌ** ፤ **(ማእከላይ ፡ ስም)** ፤ ዘይቤው ፡ ዕጨ ፣ ዕጨጌ ፤ ሱታፌ ፡ ንጉሥ ፤ ባለሚሶ ፡ መንግሥት ። ምስጢሩ ፥ ሊቀ ፡ ሀገር ፣ ሊቀ ፡ ካህናት ፣ ርእሰ ፡ አድባራት ፡ ወገዳማት ። ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ኒቅያ ፡ ሕግ ፡ ትምርቱንና ፡ ንጽሕናውን ፣ ጠባዩንና ፡ አናዎሩን ፣ አስተዳደጉን ፡ አይታ ፣ መርምራ ፥ ይደልዎ ፡ ብላ ፡ መርጣ ፣ መስክራ ፡ ባልሾመችው ፥ ሌሎች ፡ ከወገናቸው ፡ መርጠው ፡ በሚሾሙት ፥ ቋንቋውን ፡ በማታውቀውና ፡ ቋንቋዋን ፡ በማያውቅላት ፡ በባዕድ ፡ በንግዳ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ጳጳስ ፡ ታዞ ፡ ተናዞ ፡ መኖርን ፡ ስለ ፡ ወደደች ፤ ፪ኛም ፡ ክብሯንና ፡ መንበረ ፡ ክብሯን ፡ አካታ ፡ ፈጽማ ፥ ይቅርብኝ ፡ ብላ ፡ ለባዕድ ፡ መስጠትን ፡ ስለ ፡ ጠላች ፥ አፍኣዊ ፡ ስሙን ፡ መለካዊ ፡ ወይም ፡ ባስልዮስ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ሐፄጌ ፡ ብላዋለች ፡ እንጂ ፥ ውስጣዊ ፡ ስሙ ፡ ጳጳስ ፣ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ነው ። ጳጳስ ፡ ሲታጣም ፥ በግልጥ ፡ የጳጳስ ፡ ሥራን ፡ እየሠራ ፡ አቡንና ፡ ዕጨጌ ፡ ይባላል ፤ ጳጳስም ፡ ቢኖር ፥ ላገሩ ፡ እንግዳ ፥ ለሕዝቡ ፡ ባዳ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ አፈ ፡ ድዳ ፣ ቀንደ ፡ ጐዳ ፡ መስሎ ፥ ያቀረቡለትን ፡ ቅስና ፣ ዲቁና ፡ ከመሾም ፡ በቀር ፡ ሊፈርድና ፡ ሊተች ፥ ሊሰብክ ፡ ሊያስተምር ፡ አይችልምና ፥ በሕዝብና ፡ በካህናት ፡ ላይ ፡ ሥልጣኑ ፣ መብቱ ፣ ፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ወትሮ ፡ የዕጨጌው ፡ ነው ። **«ወፈታሒሰ ፡ ውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፤ አው ፡ ኤጲስቆጶስ ፤ አው ፡ ዘአትለውዎ ፡ እሙንቱ ፡ ወረሰይዎ ፡ ህየንቴሆሙ ፡ በእንተ ፡ ፍትሕ ። ይኩን ፡ ድኁነ ፡ ልሳን ፡ ወዘየአምር ፡ ነገረ ፡ ልሳን ፡ እንተ ፡ ኢትትከሀል ፡ ልሳነ ፡ ሰብእ ፡ ሚመቱ ፡ በዘይትናገሩ ፡ በበይናቲሆሙ»** ፡ (ፍ.ነ. ፥ ፵፫) ። በ"ፅግዕ" ፡ እና ፡ በ"ፅጋዕ" ፡ ዘይቤም ፡ ሲፈቱት ፥ **«ወምስማካሰ ፡ ለመንግሥትክሙ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ»** ፡ እንዳለው ፡ ኹሉ ፡ (ቄር.) ፥ መጨጊያ ፣ መከዳ ፡ ያሰኛል ። ዕጨግናን ፡ ከጵጵስና ፡ አዛምዶ ፣ አዋሕዶ ፣ አጣምሮ ፣ አስተባብሮ ፡ ያሳያል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ መከዳ ፥ ንጉሡን ፡ አማኽለው ፥ አቡኑ ፡ በቀኝ ፥ ዕጨጌው ፡ በግራ ፡ በመቀመጣቸው ፡ ይታወቃል ። አቡን ፡ ሲታጣ ፡ ግን ፥ ቀኙ ፡ የዕጨጌ ፡ ነው ። ዕጨጌነትም ፡ የተዠመረ ፡ ባ፲፱፻፳፫ ፡ (፶፫) ፡ ዓመት ፥ ይኩኖ ፡ አምላክን ፡ ቀብተው ፡ ባነገሡ ፡ በዳግማይ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። ርሳቸውም ፥ በናታቸው ፡ የነገሥታት ፡ ወገን ፥ የይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ያክሥት ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የናት ፡ ወንድም ፥ አጎት ፤ ወዲህም ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.እ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ።  ፊት ፡ በሕግ ፡ ቀሰው ፥  በኋላ ፡ መንኰሰው ፡ አቡን ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ የማይገ͘ባ ፡ መስሏቸው ፡ «አቦ ፡ ብልኀት ፥ ዕጨግነት ፡ ከሚስት» ፡ ብለዋቸዋል ።  ዳግማይ ፡ ማለትም ፥ በ፳ኛው ፡ መቶ ፥  ይህን ፡ ሐዲስ ፡ ስም ፥  «ተክለ ፡ ሃይማኖት» ፡ መባልን ፥  እንደ ፡ ያዕቆብ ፥  በጌታ ፡ ቃል ፡ ለተሰየሙት ፡ ለጻድቁና ፡ ለቅዱሱ ፥  ለታላቁ ፡ ሐዋርያ ፡ እንጂ ፥  ባ፲ኛው ፡ መቶ ፡ መንግሥትን ፡ ከድልነዓድ ፡ ወስዶ ፡ መዠመሪያ ፡ ከዛጔ ፡ ወገን ፡ ለነገሠው ፡ መራ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለተባለው ፡ ለላስታው ፡ ንጉሥ ፡ አይደለም ። በጻድቁና ፡ በዕጨጌው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ካ፫፻፶ ፡ ቢበልጥ ፡ እንጂ ፡ አያንስም ፡ (ታሪክና ፡ ገድል) ።  ጳጳስን ፡ እይ ❖

---

# ሐተታ ፡ መጻሕፍት ።

## Books Review | revue de livres

በቅርቡ ፡ ከደረሱን ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡—

- **ዲያቆን ፡ ዳንኤል ፡ ክብረት** ፤ *"ኢትዮጵያዊው ፡ ሱራፌ ፤ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሕይወት ፡ ታሪክና ፡ አስተዋፅኦ ። "* ፥  ዐዲስ ፡ አበባ ፥  2011 ፡ ዓ.ም. ፤  1081 ፡ ገጾች ።




ይህኛውን ፡ መጽሐፍ ፡ ለማተት ፡ ትንሽ ፡ ተቸግረን ፡ ነበር ። የ 1081 ፡ ገጾች ፡ ድጕሰቱ ፡ አስፈራርቶን ፡ አይደለም ።

ምናልባት ፥  ርእሱ ፡ የጻድቁ ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሕይወትና ፡ ገድል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥  ይህ ፡ ከሚጠይቀው ፡ ጥንቃቄ ፡ ጋራ ፥  የሚጠይቀው ፡ ዕውቀት ፡ ጕድሎ ፥  መልሶ ፡ ያስተቸ ፡ እንደ ፡ ኾነስ ፡ ብለን ፡ ሠግተን ፤  አንዳች ፡ የምንነቅፈው ፡ ጕዳይ ፡ ቢኖር ፥  ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡— *ምእመን ፡ ካህንን ፡ አይንቀፈው* ፡ ብላ ፡ ታስተምረናለችና ፥ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቃውንት ፡ ይዩት ፡ ብለን ፡ እንጂ ። ጥቂት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቃውንትም ፡ በመጽሐፉ ፡ ምርቃት ፡ ላይ ፥  ቡራኬ ፡ ሲሰጡ ፡ አይተን ፡ ረክተን ፡ ነበር ።

ታዲያ ፥  መጽሐፉን ፡ ገለጥ ፡ አድርገን ፡ ስንመረምረው ፥ እላይ ፡ የተነገረው ፡ እንደተያዘ ፡ ኾኖ ፥  ዝም ፡ ማለቱ ፡ ከጥቅሙ ፡ ጕዳቱ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚያመዝን ፡ መስሎ ፡ ታየንና ፥ አንባቢ ፡ እንዲጠነቀቅበት ፥  ደራሲውም ፡ ምናልባት ፡ አንዳንድ ፡ ያየናቸውን ፡ ጕድለቶች ፡ እንዲያሟላበት ፣ ስሕተት ፡ የመሰሉንንም ፡ እንዲያቃናበት ፡ ብለን ፡ የሚከተለውን ፡ ሐተታ ፡ በጽሑፍ ፡ አስፍረናል ።

ስለ ፡ ጻድቁ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ ኾነ ፥  ከርሳቸው ፡ በኋላ ፡ ስለመጡት ፡ ስለ ፡ ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፥ እንኳን ፡ 1081 ፡ ገጾች ፥  1081 ፡ መጻሕፍትም ፡ ቢታተሙ ፡ ይገ͘ባቸዋል ።

በስምንተኛው ፡ ምእትያ ፥  መቶሎሚ ፡ የተባለ ፡ በደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የእናርያ ፡ ንጉሥ ፥  በመኻከለኛው ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ዐምፆ ፡ አገር ፡ ባጠፋበት ፡ ወቅት ፥  ኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ ዐጥታ ፥  ካህናትን ፡ ማግኘት ፡ በተቸገረችበት ፡ ሰዓት ፥ እግዚአብሔር ፡ ያስነሣቸው ፡ ሐዋርያ ፡ ናቸው [7] ።  ገና ፡ በእናት ፡ ማሕፀን ፡ ኾነው ፡ በወጣላቸው ፥  ከዚያ ፡ በፊት ፡ ማንም ፡ ባልተጠራበት ፡ ስም ፥  *"ተክለ ፡ ሃይማኖት"* ፡ መባላቸውን ፡ ገድላቸው ፡ ይነግራል ።  *"ብርሃን ፡ ዘኢትዮጵያ"* ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፥  በዚያ ፡ ዘመን ፡ ክርስትናን ፡ ለደቡብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰብከውና ፡ አስተምረው ፥  አሕዛብን ፡ አጥምቀው ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ አድርገዋል ፤  ሃይማኖትን ፡ አስፋፍተዋል ፤  ሀገርንም ፡ ሀገር ፡ አሠኝተዋል ።  በዚህም ፡ ትሩፋታቸው ፥  ዝናቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ዐልፎ ፥ ቅድስናቸው ፡ በክርስቲያኑ ፡ ዓለም ፡ ተመስክሯል ።

ከርሳቸው ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥  ባ፲፫ኛው ፡ ምእትያ ፡ የተነሡት ፡ ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት [8] ፥  በታሪክ ፡ ሦስተኛው ፡ *"ተክለ ፡ ሃይማኖት"* ፡ ናቸው ።  ከርሳቸው ፡ በፊት ፥  ከጻድቁ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በኋላ ፥  የዛጔው ፡ ንጉሥ ፥  መራ͘ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ ተጠርተውበታል ።

ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፥  ከመንፈሳዊ ፡ አባትነታቸው ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ የስያሳ ፡ ወይም ፡ የ *"ፖለቲካ"* ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። ምናልባት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪክ ፡ ረቂቁን ፡

---

7 ጻድቁ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተወለዱት ፡ በ 8 ኛው ፡ ምእትያ ፥  በምሥራቅ ፡ ሸዋ ፥  በቡልጋ ፡ አውራጃ ፥  ልዩ ፡ ስሙ ፡ እቲሳ ።

8 ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተወለዱት ፡ ባ 13 ኛው ፡ ምእትያ ፥  በሰሜን ፡ ሸዋ ፥ በወግዳ ፡ ወረዳ ፥  ልዩ ፡ ስሙ ፡ ወይንጌ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የኢትዮጵያ ፡ የግዛት ፡ ፍልስፍና ፡ ያነቁ ፣ ያራቀቁ ፥ ሕዝብንም ፡ ሰብከው ፡ ባንድነት ፡ ያስነሡ ፥ አስነሥተውም ፥ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ 1262 ፡ ዓ.ም. ፡ በዐምሐራ-ሣይንት ፡ በተጠራ ፡ ሀገራዊ ፡ ሸንጎ ፥ *"ዐፄ ፡ ሥር"* ፡ የተባለውን ፡ በጽሑፍ ፡ የሚገኘውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥት ፡ በሕዝብ ፡ እንደራሴዎች ፡ ያስጸደቁ ፡ ታላቅ ፡ ሊቅና ፡ መንፈሳዊ ፡ መሪ ፡ ነበሩ ። ርሳቸው ፡ በነበሩበት ፡ ባ፲፫ኛ ፡ ምእትያ ፥ ባውሮፓ ፡ ምድርም ፡ ተመሳሳይ ፡ ሚያን ፡ የዋሉ ፡ የአኲናሱ ፡ ቅዱስ ፡ ቶማስ ፡ (St. Thomas of Aquinas) ፡ የተባሉ ፡ መንፈሳዊ ፡ አባት ፡ ተነሥተው ፥ የምዕራቡን ፡ ዓለም ፡ ሥርዐታተ ፡ መንግሥታት ፡ ባዳዲስ ፡ መሠረታት ፡ ላይ ፡ የጣለ ፡ ትምህርትን ፡ አስተምረዋል ።

በዘመናችን ፥ ከሰሜን ፡ ደቡብ ፣ ከምዕራብ ፡ ምሥራቅ ፡ በሥራ ፡ ምክንያት ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲዘዋወሩ ፥ ከሊቃውንቱ ፡ ትምህርትና ፡ መጻሕፍት ፣ ከሕዝቡም ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ የዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሥራ ፡ በዘሊቅ ፡ በጠሊቅ ፡ ያጠኑትና ፡ የመረመሩት ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ *"ርትዓዊ ፡ ኹነት"* ፡ በተሠኘው ፡ መጽሐፋቸው [9] ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡—

*ለረዥም ፡ ዘመን ፡ በተመሳሳይ ፡ አገዛዝ ፡ ሥር ፡ ሲኖር ፥ ባ 13 ኛው ፡ ምእት ፡ ዓመት ፡ ላይ ፥ ሃይማኖታዊው ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ሊቅ ፥ ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በርትዕ ፡ ፍልስፍና ፡ ሰብከው ፥ የግለኛን ፡ ባሕርያዊ ፡ መብት ፡ በሚያከብር ፡ ኪዳን ፡ መላው ፡ ሕዝብ ፡ ተባብሮ ፥ ባንድነቱ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲተዳደር ፡ አዋደው ፥ በግዴታ ፡ ይገዛው ፡ የነበረውን ፡ መንግሥት ፡ አላንዳች ፡ ደም ፡ መፋሰስ ፡ በሰላም ፡ አስወግደው ፥ ኢትዮጵያን ፡ የውዴታ ፡ ኹነት [10] ፡ አድርገው ፥ የሥሉጥ ፡ ሕዝብ ፡ ግዛት [11] ፡ (መንግሥት) ፡ ካቋቋሙ ፡ ወዲህ ፥ በኢትዮጵያ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፥ በግለኛም ፡ ኾነ ፡ በኅብረት ፥ በሰላምና ፡ በፍትሕ ፡ ውስጥ ፥ በሐራነትና ፡ በእኩልነት ፡ ጣዕም ፡ ለመኖር ፡ ቻለ ።*

ሲሉ ፡ አብራርተውልናል ።

ደራሲው ፡ ዲያቆን ፡ ዳንኤል ፡ ክብረትም ፡—

*የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሕይወት ፡ መመርመር ፡ ማለት ፡ ኢትዮጵያን ፡ መመርመር ፡ ነው"* ፡ (ገጽ ፡ XIV) ፡

በማለት ፡ ይህኑ ፡ አረጋግጠውልናል ። መጽሐፉን ፡ ለመጻፍ ፡ የተነሣሡበትን ፡ ደግሞ ፡—

*ያ ፡ ሰሞን ፥ "ዐውቃለኹ" ፡ ባዩ ፡ ኹሉ ፥ ፖለቲካን ፣ እምነትንና ፡ ዘርን ፡ እየተንተራሰ ፥ በእኒህ ፡ ጻድቅ ፡ ላይ ፡ በትሩን ፡ የሚያሳርፍበት ፡ ዘመን ፡ ነበር ። ነገሩ ፡ በጣም ፡ ነበር ፡ የሚያሳዝነኝ ። ርሳቸው ፡ የኾኑትና ፡ ሰዎቹ ፡ የሚያወሩት ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ያኽል ፡ ይለያያል ። በርግጥ ፥ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በተመለከተ ፥ የሰይጣን ፡ ወሬ ፡ ማውራት ፡ ከተዠመረ ፡ 300 ፡ ዓመታት ፡ አልፈውታል ። የፖርቱጋል ፡ ሚስዮናውያን ፡ የዠመሩትን ፡ ነው ፡ ሌሎች ፡ የቀጠሉበት ፡ [...]*

ይሉና ፡ ደራሲው ፡ ዲያቆን ፡ ዳንኤል ፡ ክብረት ፡ ሲጨምሩ ፡—

*አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ከሀገር ፡ ቤት ፡ ሊቃውንት ፡ ወገን ፡ ጠንከር ፡ ያለ ፡ ትችት ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የሰነዘሩ ፡ ሊቅ ፡ ናቸው ። የርሳቸው ፡ ትችት ፡ በዋናነት ፡ ያተኰረው ፥ ጻድቁ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ዕጨጌው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይለያያሉ ፡ በሚለው ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ነው ። ለዚህ ፡ ሐሳባቸው ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ አልሜዳ ፡ ያነሣቸውን ፡ ሐሳቦች ፡ በመያዝ ፡ የራሳቸውን ፡ ጨምረውበታል ። ይህ ፡ የአለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ መከራከሪያ ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ "ተሐድሷውያን" ፡ የሚባሉት ፡ ወገኖች ፡ ላነሧቸው ፡ ሐሳቦች ፡ መሠረት ፡ ኾነዋል ።*

በማለት ፡ በዐጸደ ፡ ነፍስ ፡ የሚገኙትን ፡ ታላቁን ፡ ሊቅ ፡ እና ፡ ሀገር ፡ አፍቃሪ ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌን ፡ ከወነጀሉ ፡ በኋላ ፥ የግፍ ፡ ግፍ ፥ መናፍቃን ፡ ከተከሉብን ፡ አንግዳ ፡ ልማድም ፡ ጋራ ፡ ያነካኳቸዋል ።

አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ (1862-1936 ፡ ዓ.ም.) ፡ የሚታወቁበትን ፡ የግእዝ-ዐማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ያላጠናና ፡ ያልመረመረ ፥ ያልተማረበት ፣ ያልሠራበትና ፡ ያልተጠቀመበት ፡ ብዙ ፡ ዘመናዊ ፡ ምሁር ፡ አይገኝም ። ስለሊቁ ፡ ትሩፋት ፡ መዘርዘሩ ፡ ይህ ፡ ቦታውም ፡ ምክንያቱም ፡ አይኾንም ። እግዚአብሔር ፥ ሥራቸውን ፡ ዐውቆ ፥ በተወለዱ ፡ በ 75 ኛ ፡ ዓመታቸው ፡ ግንቦት ፡ 24 ፡ ቀን ፡ 1936 ፡ ዓ.ም. ፡ (ልክ ፡ የዛሬ ፡ 75 ፡ ዓመት) ፡ ዐርፈው ፥ አጸድቃኑ ፡ ገዳም ፡ እደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ተቀብረዋል ። ዛሬ ፥ ስማቸው ፡ አላግባብ ፡ እንዲህ ፡ መነሣቱ ፥ አንድም ፡ ያሳዝናል ፥ አንድም ፡ ጕዳዩ ፡ የቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ማንነት ፡ ብቻ ፡ አለመኾኑን ፡ ይጠቍማል ።

የኢጣልያ ፡ ፋሺስት ፡ ወረራን ፡ በገሃድ ፡ በመቃወማቸው ፡ ላምስት ፡ ዓመት ፡ እጨለማ ፡ ቤት ፡ ዐይናቸው ፡ እስኪጠፋ ፡ የታሰሩትን ፡ ሰማዕት ፥ ባልሠሩት ፡ ወንጀል ፡ ስማቸውን ፡ ማጥፋት ፡ ለምን ፡ አስፈለገ ፧ ያሳሰሯቸውስ ፡ ዲያቆን ፡ ዳንኤል ፡ ክብረት ፡ የሚጠቃቅሱት ፥ የኢትዮጵያን ፡ ቅርሳቅርስ ፡ የዘረፈው ፡ ፋሺስቱ ፡ ኤንሪኮ ፡ ቼሩሊና ፡ ግብር ፡ ዐበሮቹ ፡ አይደሉምን ፧

*"ሐፄጌ"* ፡ (*"ዕጨጌ"* ፡ ባማርኛ) ፡ ስለሚለው ፡ የግእዝ ፡ ቃል ፡ የሰጡት ፡ ፍች ፡ *"ከታሪክ ፡ ዐምድ"* ፡ በተባለው ፡ ዐምድ ፡ በዚህ ፡ መጽሔት ፡ ዕትም ፡ (ቍ.2011-002 ፥ ገጽ ፡ 11) ፡ ወጥቷል ፤ አንባብያን ፡ አንድ ፡ አፍታ ፡ እንዲያነቡት ፡ እንጋብዛለን ።

9 ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፤ ርትዓዊ ፡ ኹነት ። 1988 ፡ ዓ.ም. ፤ ገጽ ፡ 9 ።
10 ኹነት ፤ የአካል ፡ ህላዌ ፣ እነት ፣ መኾን ፡ (በግእዝ ፡ "ኩነት") ።
11 ሥሉጥ ፤ ሥልጡን ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፥ መብትና ፡ ግዴታውን ፡ የሚያውቅ ፥ ሿሚ ፡ ሻሪ ፥ እግዚእ ፥ ገዥ ፥ ጌታ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፥ በምሁር ፡ አንደበትና ፡ ብርዕ ፡ የነገሩት ፡ ቃል ፡ ካሳማኝነትም ፡ በላይ ፥ በመሳ ፡ ኢትዮጵያ ፥ ከሊቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፡ የሚነገረውንና ፡ የሚታመነውን ፡ እንጂ ፥ ከ300 ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ መጥተው ፡ ከነበሩ ፡ ፖርቱጋሎች ፡ ሳይቸግራቸው ፡ የተበደሩት ፡ ግብዝ ፡ ዕውቀት ፡ አይደለም ። ጻድቁ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፥ እንደ ፡ ጻድቁ ፡ አቡነ ፡ አረጋዊና ፡ እንደ ፡ ጻድቁ ፡ አቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (አቦ) ፥ በምንኵስና ፡ ኖረው ፡ በምንኵስና ፡ ያረፉ ፡ መንፈሳዊ ፡ አባት ፡ ናቸው ። ከአቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ወይ ፡ ከአቡነ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፦ *"እወለዳለኹ"* ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ አይገኝም ። ከዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ግን ፡ የሚወለዱ ፡ የካህን ፡ ዘር ፡ የኾኑ ፡ ቤተሰቦች ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ አሉ ፤ እነዚህ ፡ ሕያዋን ፡ ምስክሮች ፡ ናቸው ። አንዳንዶቻችን ፡ ብንጠየቅ ፥ በግላችን ፡ የምናውቃቸው ፡ ጥቂት ፡ ቤተሰቦች ፡ አይጠፉም ። ዕጨጌ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያገቡ ፡ የወለዱ ፡ ቄስ ፡ ኾነው ፡ ኖረው ፥ በኋላ ፡ ዘመን ፡ መንኵሰው ፡ እስከዕጨጌነት ፡ ማዕርግ ፡ ደርሰዋል ። ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ይበልጥ ፡ ሊመረመር ፡ እንጂ ፡ በ*"ቍጫት"* ፡ ሊገፋ ፡ አይገባም ፤ ታሪክ ፡ ነው ። የታሪክ ፡ ሰው ፡ ማስረጃን ፡ ሳይንቅ ፡ ሊመረምር ፡ እንጂ ፥ እንደ*"ማስታወቂያ ፡ ሚኒስቴር"* ፡ ለፋፌ ፡ ሊያስተባብል ፡ አይገባውም ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፥ ያለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌን ፡ ስም ፡ በማጥላላት ፥ *"የአቡጊዳን ፡ የፊደል ፡ ተራ ፡ ያመጡት ፡ ከኮሎኒያሊስቶች ፡ ቀድተው ፡ ነው"* ፡ የሚል ፡ ፍጹም ፡ ከእውነት ፡ የራቀ ፡ ቃል ፡ በሌላ ፡ ኹኔታና ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ተነግሮ ፣ ተጽፎ ፡ ነበር ። አኹንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከሊቅ ፡ እስከ ፡ ደቂቅ ፡ የሚያውቀውን ፡ እውነት ፡ ካድ ፡ አድርገው ፥ ፊደል ፡ ከተቀረጸ ፡ ከብዙ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ አንሥቶ ፡ ትውልዶች ፡ ፊደል ፡ የቈጠሩበትን ፡ ጥንታዊ ፡ የአቡጊዳን ፡ ተራ ፥ በ20ኛው ፡ ምእትያ ፡ ጣሊያን ፡ ያመጣው ፡ የፊደል ፡ ተራ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከመቅጠፍ ፡ የባሰ ፡ ምን ፡ ቅጥፈት ፡ ይገኛል ፨ *"ኢትዮጵያ ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ታሪክ ፡ ያላት ፡ ሀገር ፡ ናት"* ፡ የሚለው ፡ ሌላው ፡ የምናውቀው ፡ የዘመኑ ፡ ቅጥፈት ፡ ምናልባት ፡ ይተካከለው ፡ ይኾናል ። የፊተኛውንም ፡ ይህንም ፡ ሐሰት ፡ ለማሳመን ፥ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ የ*"ሦስት ፡ ልደት"* ፡ ሃይማኖት ፡ ተከታይ ፡ ነበሩ ፡ የሚለውን ፡ ማጥላሊያ ፡ ያስቀድሙላቸዋል ። እውን ፡ Oxford English Dictionaryን ፡ ገዝተን ፡ የምንሠራበት ፡ *"ኹለት ፡ ልደት"* ፡ የሚሉ ፡ የተዋሕዶ ፡ ሊቃውንት ፡ ስለሠሩት ፡ ነውን ፨ ዲያቆን ፡ ዳንኤል ፡ ክብረትስ ፡ ቢኾኑ ፥ ዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድን ፡ እያጀቡ ፥ በእየጉባኤው ፡ ሲያስተናብሩላቸውና ፡ ጉባኤተኛውን ፡ ሲያጋፍሩላቸው ፥ ከቶ ፡ የጸንጠቀስጤ ፡ እንጂ ፡ የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ተከታይ ፡ አለመኾናቸውን ፡ ዐጥተውት ፡ ይኾን ፨ አላጡትም ፥ አልዘነጉትም ፤ *"ሃይማኖት ፡ የግል ፤ ሀገር ፡ የጋራ"* ፡ ብለው ፡ እንጂ ።

የ*"ኹለት ፡ ልደት"* ፡ እና ፡ የ*"ሦስት ፡ ልደት"* ፡ ሃይማኖታዊ ፡ ክርክር ፥ ልክ ፡ የዛሬ ፡ 141 ፡ ዓመት ፥ በቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ጉባኤ [12] ፡ በ*"ኹለት ፡ ልደት"* ፡ ርታታ ፡ አንዴ ፡ ለመቼውም ፡ ስለተደመደመ ፥ የፊደልንና ፡ የቋንቋን ፣ የስያሳንና ፡ የታሪክን ፡ ጉዳዮች ፡ ማየት ፡ ያለብን ፡ በራሳቸው ፡ እውነት ፡ እንጂ ፡ በደራሲው ፡ ወይ ፡ በተናጋሪው ፡ እምነትና ፡ ማንነት ፡ አንጻር ፡ መኾን ፡ የለበትም [13] ።

ይህን ፡ በመሰለው ፡ ማጥላሊያ ፡ ቀድሞ ፡ መሸብለቅ ፥ *"ዥብ ፡ ሊገድሉ ፡ ባህያ ፡ ይጠጉ"* ፡ እንዲሉ ፥ ሌላ ፡ ዒላማ ፡ ቢኖር ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ልንጠረጥር ፡ እንገደዳለን ። ኢትዮጵያዊ ፡ ሥልጣኔያችንና ፡ መንኰራኵሩ ፡ አቡጊዳ-ፊደላችን ፣ መስፋፊያ ፡ ጎዳናውም ፡ ግእዝ-ዐማርኛችን ፡ ብዙ ፡ ባላንጣና ፡ ጠር ፡ አሉባቸውና ፥ ለማንኛውም ፡ ነቅቶ ፡ መጠበቁ ፡ አይከፋም ።

ዘመኑ ፡ የ*"ሴራ"* ፡ ዘመን ፡ መኾኑ ፡ ቢታመንም ፥ ደራሲው ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ የክዳት ፡ ተግባር ፡ ይሳተፋሉ ፡ ብለን ፡ ለቅጽበት ፡ እንኳ ፡ አንጠረጥርም ። ምናልባት ፡ ግን ፥ ሳያውቁ ፡ ተመችተውለት ፡ ይኾናልና ፥ መጽሐፋቸውን ፡ ዳግመኛ ፡ የሚያሳትሙት ፡ ቢኾን ፥ ይህን ፡ ጥንቃቄ ፡ የጐደለውንና ፡ ትርፍ ፡ የኾነ ፡ አስተያየት ፡ ለቅመው ፡ አስወግደው ፥ እውነቱ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ በማተኰር ፥ ሊያከራክረን ፡ የማይገባውን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ታሪክና ፡ ማንነት ፡ በሚያሳምነን ፡ መንገድ ፡ ለማጣራት ፡ ቢደክሙልን ፡ ባለውለታቸው ፡ እንኾናለን ።

የፊደል ፡ ነገር ፡ ከተነሣ ፡ ዘንዳ ፥ በመጽሐፋቸው ፡ የሚታዩትንም ፡ ዐያሌ ፡ የፊደል ፡ ስሕተትና ፡ የዝግጅት ፡ ጉድለት ፥ ለኢትዮጵያ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ እድገት ፡ ሲባል ፥ ደራሲው ፡ ዐብረው ፡ ቢያረቱልን ፥ እጅጉን ፡ እናመሰግናቸዋለን ።

በተረፈ ፥ መጽሐፉ ፡ ብዙ ፡ የተደከመበት ፡ ነው ። በርከት ፡ ያሉ ፡ መረጃዎችንና ፥ በየጉዳዩ ፡ የደራሲውን ፡ የግል ፡ አስተያየቶች ፡ ያካፍላል ፤ እንዲሁም ፥ በቀላሉ ፡ የማይገኙ ፡ የታሪክ ፡ መዛግብትን ፡ መገኛዎች ፡ ይጠቍማል ። እላይ ፡ የተገለጠው ፡ ነቀፋ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ኾኖ ፥ የታሪክ ፡ ተማሪዎችና ፡ ተመራማሪዎች ፡ ጥቅም ፡ ያገኙበታል ❖

---

12 ግንቦት ፡ 18 ፡ ቀን ፡ 1870 ፡ ዓ.ም.

13 ይህንም ፡ ሲያስተምሩን ፥ ታላቁ ፡ የተዋሕዶ ፡ ሊቅ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ጀንበሬ ፡ ***መጽሐፈ ፡ ቅኔ*** ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ (ገጽ ፡ 25-30) ፡ ስለአለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ የቋንቋ ፡ ልህቅና ፡ መስክረው ፥ ትምህርታቸውንም ፡ በተጠቀሰው ፡ መጽሐፋቸው ፡ በገቢር ፡ አሳይተውናል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# ጥርዮታዊ ፡ ትንታኔ ፡፡

Economic Analysis | Analyse économique



## ልማት ፣ እድገትና ፡ ንረት ፡ በዘመናችን ፡ ኢትዮጵያ ።

---

የጥጋብ ፡ ዘምንና ፡ የረኃብ ፡ ዘመን ፡ የምንላቸው ፡ የዘመን ፡ መንቲያዎች ፥ አለመፈራረቅ ፥ አንድጋ ፡ መታየታቸው ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመሳሰሉት ፡ ችግረኞች ፡ ሀገሮች ፡ እንጂ ፥ በለሙት ፡ ሀገሮችስ ፡ መፈራረቃቸውም ፡ እንኳ ፡ ቀርቷል ። እለሙት ፡ ሀገሮች ፡ ዘንድ ፡ የሚታወቀው ፡ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ ኾኗል ፤ ይህም ፡ - ፡ የጦርነቱን ፡ ዘመን ፡ ትተን ፡ - ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ዐልፎታል ። እነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ጕዳዩ ፡ የሚተነተንበት ፡ ቃላትም ፡ የጥጋብ ፡ መለኪያ ፦ "ልማት" ፣ "እድገት" ፡ እና ፡ "ንረት" ፡ ኾነዋል ።

ችግረኞች ፡ ሀገሮች ፡ አልን ፡ እንጂ ፥ ድኾች ፡ ሀገሮች ፡ አላልንም ፤ ልዩነት ፡ አለውና ። "ድኻ ፡ ሀገር" ፡ የሚባለው ፡ በተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ የተበደለ ፥ ከሰፈረበትና ፡ በድኽነት ፡ ከሚያድርበት ፡ ነዋሪ ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ የማይችል ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ማለት ፡ ነው ። "ችግረኛ ፡ ሀገር" ፡ ደግሞ ፥ በተፈጥሮ ፡ የታደለው ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ እያለው ፥ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግሮች ፡ ምክንያት ፡ ሀብቱን ፡ በሚገባ ፡ ማልማት ፡ የተሳነውና ፡ አብዛኛው ፡ ነዋሪ ፡ በችጋር ፡ የሚማቅቅበትን ፡ ሀገር ፡ ያመለክታል ። ኢትዮጵያ ፡ በዚህኛው ፡ በችግረኞች ፡ ሚና ፡ ትገኛለች ።

"ልማት" [14] ፣ "እድገት" [15] ፣ "ንረት" [16] ፡ የምንላቸው ፡ ቃላት ፡ በጥርዮትኛ ፡ ዋና ፡ ቦታ ፡ አላቸው ። ጥርዮትኛም ፡ ለስሙ ፡ "science" ፡ ቢባልም ፡ ቅሉ ፥ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ማኅበራውያን ፡ የጥናት ፡ መስኮች ፥ የሰውንና ፡ የሰብአዊ ፡ ማኅበርን ፡ ዓለማዊ ፡ ህላዌ ፡ የሚመረምር ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ፍጹምነት ፡ የለውም ። የጥርዮትኛ ፡ ድምዳሜዎች ፥ ኹልጊዜም ፡ ቢኾን ፥ በሽልግና ፡ በመላ ፡ ምት ፡ መኻል ፡ የሚሰጡ ፥ አለዚያም ፡ ከስያሳዊ ፡ ጥቅም ፡ አንጻር ፡ የሚሰበኩ ፡ ናቸውና ፥ ምንም ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ "ሒሳብ" ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ አስተማማኝ ፡ አይኾኑም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ ልማትም ፡ እድገትም ፡ ንረትም ፡ እንዳጥኛቸውና ፡ እንደ ፡ ሰባኪያቸው ፡ አስተያየት ፡ የተለየ ፡ ፍች ፡ ሊሰጣቸው ፡ ይችላል ። ለመነሻ ፡ ያኽል ፥ ይበልጥ ፡ የሚጠቀሱትን ፡ ፍቾች ፡ አስቀድመን ፡ እናመልክት ፦

- **ልማት** ፤ በጠቅላላው ፡ የሰው ፡ ልጅን ፡ የኑሮ ፣ የክብረትና ፡ የነጻነት ፡ ደረጃን ፡ የማሳደግ ፡ ኺደት ።
- **እድገት** ፤ ያንድ ፡ ምጥራይ [17] ፡ አጠቃላይ ፡ የማምረት ፡ ዐቅም ፡ ማደግ ።
- **ንረት** ፡ ወይም ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፤ ያንድ ፡ ምጥራይ ፡ አጠቃላይና ፡ ተከታታይ ፡ የዋጋ ፡ ደረጃ ፡ እድገት ፥ ወይም ፡ የገንዘብ ፡ ምንዛሪ ፡ ውድቀት ።

መደንገጉ ፡ መልካም ፡ ኾኖ ፥ ሐሳቡን ፡ ከእውኑ ፡ ጋራ ፡ ለማገናኘት ፡ ሲሞክሩ ፥ በሥርዐት ፡ በጊዜና ፡ በቦታ ፡ የሚታየው ፡ ልዩነት ፡ በንጽጽር ፡ ደረጃ ፡ የማይታለፍ ፡ መሰናክልን ፡ ይደቅናል ።

በልማት ፡ ረገድ ፥ ጕዳዩ ፡ ከአኃዝ ፡ ይልቅ ፥ ከኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነጻነትና ፡ እንደ ፡ ሰብአዊ ፡ መብት ፡ ያሉ ፡ የኑሮ ፡ ዕሴቶችን ፡ ወይም ፡ ክብረቶችን ፡ ያገናዝባል ። ታዲያ ፡ የስዊስን ፡ ልማት ፡ ከቻይና ፡ ልማት ፡ ጋራ ፡ እንዴት ፡ እናስተያየው ፡ ይኾን ፧

በእድገትና ፡ በዋጋ ፡ ንረት ፡ ረገድ ፥ በአኃዝ ፡ ለቀማ ፡ የሚታዩት ፡ የድርጅት ፣ የዐቅም ፣ የስልት ፣ የታማኝነት ፡ ልዩነቶች ፡ አህጉራዊ ፡ የእድገት ፡ ንጽጽርን ፡ ዋጋ ፡ ያሳጡታል ። ያውሮፓ ፡ ኅብረት ፡ ጥርዮት ፡ በ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ ባማካይ ፡ ባ 1.9 ፡ በመቶ ፡ አደገ ፡ ቢባል ፥ የኅብረቱ ፡ ሀገሮች ፡ የአኃዝ ፡ ለቀማ ፡ ተቋማት ፡ በዐቅምም ፡ በደንብም ፡ በስልትም ፡ በሥልጠናም ፡ በነጻነትም ፡ ተመሳሳይ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኙ ፥ አስተማማኝ ፡ በሚባል ፡ ኹኔታ ፡ ልቅሞቻቸው ፡ ተጠናቅረው ፡ ዓመታዊ ፡ አማካይ ፡ እድገቱን ፡ ማስላት ፡ ይቻላል ። ኢትዮጵያን ፡ በመሰሉ ፡ ሀገሮች ፡ ዘንድ ፡ ኹኔታው ፡ ፈጽሞ ፡ ይለያል ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥታውያን ፡ የአኃዝ ፡ ለቀማ ፡ ተቋማት ፡ በሰውና ፡ በድርጅት ፡ በባጀት ፡ ዐቅምም ፡ የተቸገሩትን ፡ ያኽል ፡ ከስያሳዊ ፡ ተፅእኖ ፡ ስለማይነጹ ፥ ተቋማቱ ፡ ከተመሠረቱበት ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ ይፋ ፡ የሚያወጧቸው ፡ አኃዞች ፡ ታማኝነት ፡ የላቸውም ፡ ቢባል ፡ ማጋነን ፡ አይኾንም ።

ታዲያ ፥ በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ የኢትዮጵያን ፡ አጠቃላይ ፡ ልማትና ፡ እድገት ፥ በየጊዜው ፡ የሚታዩትንም ፡ የዋጋ ፡ ንረቶች ፡ እንደምን ፡ እንለካቸውና ፡ እንወቃቸው ፧ ሌላ ፡ ኹለተኛ ፡ መንገድ ፡ ይኖር ፡ ይኾን ፧ ወይስ ፡ ከአኃዛዊ ፡ ልክ ፡ ይልቅ ፡ የጥራት ፡ ልክ ፡ የልማትና ፡ የእድገትን ፡ ምጣኔ ፡ የተሻለ ፡ ያስገነዝበን ፡ ይኾን ፧

*(ይቀጥላል ። )*

---

14 ልማት | development | développement
15 እድገት | growth | croissance
16 ንረት | inflation
17 ምጥራይ | economic system | système économique


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

| አንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መልክአ ፡ ምድራውያንና ፡ ክፍለ ፡ ሀገራውያን ፡ አኀዛውያን ፡ ልቅሞች ፡ (2011 ፡ ዓ.ም.) ፡፡ | | |
|---|---|---|
| ክፍል | መጠን | ደረጃ ፡ (ከዓለም) |
| መልክአ ፡ ምድራዊ ፤ | | |
| የወለል ፡ ስፋት ፤ | 1.3 ፡ ሚልዮን ፡ ኪ.ሜ $^2$ [18] ፡ (ባሕር ፡ ምድርን ፡ ጨምሮ) | 20 ኛ ፡ (ከዓለም) |
| ደፈር ፤ | ራስ ፡ ደጀን ፡ 4533 ፡ ሜ. ፡ ከፍታ | 5 ኛ ፡ (ካፍሪቃ) |
| ሊታረስ ፡ የሚችል ፡ መሬት | 78 ፡ ሚ.. ፡ ሄክታር ፡ (60%) | |
| የሚታረስ ፡ መሬት | 11 ፡ ሚ.. ፡ ሄክታር ፡ (14%) | |
| የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ (ኢትዮጵያ) ፤ | 107 ፡ ሚ.. ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፥ 3 ፡ ሚ.. ፡ በውጭ ፡ ሀገር ፡ (በ 1948 [19] ፡ ዓ.ም. ፡ ከነበረበት ፡ 35 ፡ ሚ.. ፥ በ 1.8% ፡ አማካይ ፡ ዓመታዊ ፡ ባሕርያዊ ፡ እድገት ፡ ሲሰላ) | 12 ኛ ፡ (ከዓለም) |
| የሕዝብ ፡ አማካይ ፡ ባሕርያዊ ፡ እድገት ፡ በዓመት ፤ | 1.80% (2.5% ፡ ለዐዲስ ፡ አበባ) | |

| አንዳንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መልክአ ፡ ምድራውያንና ፡ ክፍለ ፡ ሀገራውያን ፡ አኀዛውያን ፡ ልቅሞች ፡ (2011 ፡ ዓ.ም.) ፡፡ | | | |
|---|---|---|---|
| ክፍለ ፡ ሀገር ፤ | የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ በሚልዮን ፤ | | + ፡ መጤ<br>- ፡ ኼያጅ |
| | 1948 ፡ ዓ.ም | 2010 ፡ ዓ.ም. | |
| መናገሻ ፡ አውራጃ ፡ (ዐዲስ ፡ አበባ) ፤ | 1.7 (0.8) | 7.7 (4.0) | +2.5 ፡ ሚ.. |
| ሸዋ ፤ | 5 | 15 | +2 ፡ ሚ.. |
| ወሎ ፤ | 4.5 | 11.5 | -2 ፡ ሚ. |
| ጐንደር ፤ | 4 | 11 | -1 ፡ ሚ. |
| ጐጃም ፤ | 3.8 | 12 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| ትግራይ ፤ | 3 | 7 | -2 ፡ ሚ.. |
| ሲዳሞ ፤ | 2.3 | 7.5 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| ሐረርጌ ፤ | 1.9 | 6.5 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| ጋሞ ፡ ጎፋ ፤ | 1.9 | 6 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| ከፋ ፤ | 1.8 | 6 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| ጎሩሲ ፤ | 1.5 | 5 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| ወለጋ ፤ | 1.2 | 4 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| ባሕር ፡ ምድር ፤ | 1.2 | 2 | -1.5 ፡ ሚ.. |
| ኢሉባቦር ፤ | 1 | 3.5 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| ባሌ ፤ | 1 | 3.5 | +0.5 ፡ ሚ.. |
| እውጭ ፡ ሀገር ፡ የሚኖሩ ፤ | 0.2 | 3 | |
| ባዕዳን ፡ (ስደተኞችን ፡ ጨምሮ) ፤ | 0.2 | 1 | |
| ድምር ፤ | 36 | 111 | |

18 ሚልዮን ፡ ኪ.ሜ $^2$ ፤ ሚልዮን ፡ ኪሎሜትር ፡ ማእዘን ፡ ($km^2$) ፡፡

19 ለ 1948 ፡ ዓ.ም. ፡ በሀገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ የተሰላው ፡ የሕዝብ ፡ መጠን ፡ 35 ፡ ሚልዮን ፡ ቢኾንም ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ትእዛዝ ፡ 22 ፡ ሚልዮን ፡ ተብሎ ፡ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ እንዲተላለፍ ፡ ተደርጓል ፡፡ *ሥልጡንሕዝብና ፥ ቍ.1989-008 ን ፡ ይመለከቷል ፡፡*

# ማሳሰቢያ | Notice

## የኢንተርኔት ፡ አገልግሎት ፡ ክልከላ ፡፡

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ላለፉት ፡ ወራት ፡ ከኢንተርኔት ፡ አገልግሎት ፡ በተደጋጋሚና ፡ አላግባብ ፡ በመወገዱ ፡ ምክንያት ፡ ሲቸገር ፡ ከርሟል ፡፡

በብሪታንያ ፥ የኢንተርኔት ፡ ግንኙቱ ፡ እየተጠለፈበትና ፡ እየተቈራረጠበት ፥ መርበቢያውን ፡ መከባከብም ፡ ኾነ ፡ ማዘመን ፡ ሳይቻለው ፡ ቀርቷል ፡፡

ከኢንተርኔት ፡ ግንኙቱም ፡ ባሻገር ፥ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የሚገኘውን ፡ slttunhzb.net ፡ መርበቢያውን ፡ ለማዘመን ፡ የ FTP ፡ ማዝለቂያው ፡ መሥመር ፡ ባከራዩው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ኩባንያ ፡ አለምክንያት ፡ ተዘግቶበት ፡ ኖሮ ፥ ከጥቂት ፡ ሳምንታት ፡ ጭቅጨቃ ፡ በኋላ ፥ ኩባንያው ፡ ስሕተቱን ፡ አምኖ ፡ የ FTP ፡ መሥመሩን ፡ መልሶ ፡ ከፍቶለታል ፤ ፊቱኑ ፡ የዘጋበትም ፡ ምክንያት ፡ ስሕተት ፡ መኾኑን ፡ በማመልከት ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፥ በደረሰው ፡ ማዘኑን ፡ ገልጿል ፡፡ ኾኖም ፥ እስከዚህቹ ፡ ዕለት ፡ ድረስ ፡ የማዘመን ፡ ሙከራዎቻችን ፡ ኹሉ ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ይከሽፉብን ፡ ነበር ፤ ኩባንያውም ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አልሰጠንም ፡፡

እጀርመን ፡ አገር ፡ ከሚገኘው ፡ የእ-ጦማር ፡ አገልግሎታችንም ፥ እንደዚሁ ፥ ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ተወግደን ፡ ከመቈጣጠሪያ ፡ ሰሌዳውም ፡ ታግደን ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ ቈይተናል ፡፡ መጨረሻውን ፥ ይህም ፡ ድርጅት ፡ በስሕተት ፡ እንዳገደን ፡ አምኖ ፥ እገዳውን ፡ ቢያነሣም ፥ የእ-ጦማር ፡ ሒሳቦቻችንን ፡ የምስጢር ፡ ቃል ፡ የመለወጥ ፡ መብታችንን ፡ ስለ ፡ ገደበብንና ፥ በጠቅላላው ፡ ባሳየው ፡ ፍጹም ፡ ትዕቢት ፡ የተሞላበት ፡ አመላለስ ፡ ምክንያት ፥ የእ-ጦማር ፡ መርበቢያችንን ፡ ከጀርመኑ ፡ ድርጅት ፡ አንሥተን ፡ ዳንማርክ ፡ ወደሚገኝ ፡ ሌላ ፡ ድርጅት ፡ አዛውረነዋል ፡፡

ዐዲሱም ፡ የእ-ጦማር ፡ አድራሻችን ፡—

sh1@ttomar.net

መኾኑን ፡ በትሕትና ፡ እናሳስባለን ፡፡

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡፡

### Internet Service Denial

For the past several months, the ECDU has been severely hampered by illegitimate denials of Internet services.

The Internet connections, from our headquarters in the United Kingdom, had been intermittently

### Déni de Service Internet

Durant les mois passés, l'UCDE a été sévèrement entravé dans son travail par des dénis injustifiés de services Internet.

Les connections Internet, depuis son siège au Royaume Uni, étaient constamment entre-coupées,


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡፡

interrupted to a point where it had become impossible for us to administer our website slttunhzb.net.

Beyond the issue of Internet connection, the web-hosting company based in France which hosts our web-site, had for some unknown reason denied us FTP-access, thereby preventing us from updating our website. This went on for several weeks, before the company recognised finally the mistake, stated it was sorry, and re-instated FTP-access. However, despite successful uploads, the webpages failed to be updated for many more days. The company did not give any explanation.

The German company which hosts our email accounts web-site, also prevented us from accessing them as well as our control panel for several months, before recognizing that this was a mistake. But refused us very arrogantly all possibility of changing our passwords. We have since awarded the web-hosting service for our e-mail accounts to a Danish company.

Our new e-mail address is now:

sh1@ttomar.net

the Secretariat of the Provisional Executive Council, ECDU.

à tel point qu'il nous est devenu impossible de gérer notre site Internet slttunhzb.net, et d'échanger des courriels.

Par delà la question de connections Internet, la société d'hébergement de notre site qui est basée en France, nous a refusé tout accès FTP, pour des raisons qui nous sont inconnues, compromettant ainsi les mises à jour du site. Ceci dura plusieurs semaines, avant que la société ne reconnaisse son erreur avec regret, et ne ré-institue l'accès FTP. Cependant, durant plusieurs jours encore, toutes nos tentatives de mise à jour de nos pages toiles échouaient. La société ne nous a toujours pas donné d'explication.

La société allemande qui gérait notre site de comptes courriels nous empêcha, elle aussi, de les accéder ainsi que notre panneau de configuration durant plusieurs mois, avant de reconnaître que cela était dû à une erreur. Cependant, elle nous refuse toujours avec arrogance toute possibilité de changer nos mots de passe. Nous avons depuis transféré le service d'hébergement vers une société danoise.

Notre nouvelle adresse courriel est désormais:

sh1@ttomar.net

Le Secrétariat du Conseil Exécutif Provisoire, UCDE.

# የሰብኣውያን ፡ መብቶች ፡ ብሔራዊ ፡ ድንጋጌ ።

Universal Declaration of Human Rights | Déclaration universelle des droits de l'homme

## አንቀጽ ፡ 2 | Article 2

የዘር ፣ የቀለም ፣ የጾታ ፣ የቋንቋ ፣ የሃይማኖት ፣ የግዛት ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ አስተያየት ፣ የሀገራዊ ፡ ወይም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኣዊ ፣ የሀብት ፣ የትውልድ ፡ ወይም ፡ የደረጃ ፡ አንዳች ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፥ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ በታወጁት ፡ መብቶችና ፡ ነጻነቶች ፡ ኹሉ ፡ ሊ መ ካ ፡ ይችላል ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ አባል ፡ በኾነለት ፥ ሐራም ፡ ኾነ ፣ በዐደራነት ፡ የተሰጠ ፣ ራሱን ፡ የማይገዛም ፡ ኾነ ፣ አንዳች ፡ የእግዚእና ፡ እግድ ፡ ያለበት ፡ ሀገርም ፡ ኾነ ፡ ብሔር ፡ (ምድር) ፥ በግዛት ፣ ወይ ፡ በሥልጣን ፣ ወይም ፡ በአህጉራዊ ፡ ደረጃ ፡ መሠረት ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ልዩነት ፡ አይደረግበትም ።

Everyone is entitled to all the rights and freedoms set forth in this Declaration, without distinction of any kind, such as race, colour, sex, language, religion, political or other opinion, national or social origin, property, birth or other status. Furthermore, no distinction shall be made on the basis of the political, jurisdictional or international status of the country or territory to which a person belongs, whether it be independent, trust, non-self-governing or under any other limitation of sovereignty.

Chacun peut se prévaloir de tous les droits et de toutes les libertés proclamés dans la présente Déclaration, sans distinction aucune, notamment de race, de couleur, de sexe, de langue, de religion, d'opinion politique ou de toute autre opinion, d'origine nationale ou sociale, de fortune, de naissance ou de toute autre situation.
De plus, il ne sera fait aucune distinction fondée sur le statut politique, juridique ou international du pays ou du territoire dont une personne est ressortissante, que ce pays ou territoire soit indépendant, sous tutelle, non autonome ou soumis à une limitation quelconque de souveraineté.

## አንቀጽ ፡ 19 | Article 19

ሰው ፡ ኹሉ ፥ ያስተያየትና ፡ አስተያየትን ፡ የመግለጽ ፡ ነጻነት ፡ አለለት ፤ ይህም ፡ መብት ፥

- ማንም ፡ ጣልቃ ፡ ሳይገባበት ፡ አስተያየትን ፡ ለራሱ ፡ የማብጀት ፡ መብትንና ፥
- ከማንኛውም ፡ ማወራኛ ፥ አንዳችም ፡ ጠረፍ ፡ ሳያግደው ፥ መረጃንና ፡ ሐሳብን ፡ የመቀባበል ፡ መብቱን ፡ ይጨምራል ።

Everyone has the right to freedom of opinion and expression; this right includes freedom to hold opinions without interference and to seek, receive and impart information and ideas through any media and regardless of frontiers.

Tout individu a droit à la liberté d'opinion et d'expression, ce qui implique le droit de ne pas être inquiété pour ses opinions et celui de chercher, de recevoir et de répandre, sans considérations de frontières, les informations et les idées par quelque moyen d'expression que ce soit.



©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# አስተያየት | Opinion

## *The BBC's very own fake news!*

*The BBC are once again at it! Broadcasting what I can only call their very own fake news for the 57th year running:*

*"Emperor Haile Sellassie had annexed Eritrea in 1962, against the will of the Eritrean people!"*

*I mention here the BBC because they are, to my knowledge, one of the few media groups anywhere in the World to consistently remind their listeners of this particular piece. Others have long chosen to avoid it, as it is highly dubious to say the least, or because it has lost any relevance today, and more importantly because the end result of independence has been catastrophic for everyone, including the West.*

*Returning to the "fake news" side of the issue: Emperor Haile Sellassie did not "annex" Eritrea; he did not need to do so. It was the democratically elected Eritrean parliament, the Bayto, which in 1962 unanimously voted the motion calling for the pure and simple reunification of Eritrea with the motherland Ethiopia. The Emperor merely enacted their democratic decision into law by signing the proclamation order on the 14th of November of that same year. Eritrea had in those days a proper Parliament (which it never had since "independence"), a proper Constitution (which it never had since "independence"), proper elections too (which it never had since "independence").*

*The British monarch Queen Elizabeth II visited Ethiopia in 1965, and on the same occasion honoured the inhabitants of Eritrea – now the 14th Province of Ethiopia – by paying them a visit, to their great satisfaction (footages are available, courtesy of Youtube.com).*

*We may accuse emperor Haile Sellassie of many misdeeds, including autocracy; but "annexation of Eritrea" does simply not stand scrutiny. True, there were regional and global powers which, for their own geo-political gains, opposed the reunification of Eritrea with Ethiopia, as this would give anti-colonialist Ethiopia direct access to the Red Sea. These inimical or even adversarial forces did succeed finally in achieving the "independence" of Eritrea in 1995; but this has since turned into a nightmare situation for all involved; especially for the hundreds of thousands of Eritrean families that have simply disintegrated through death, human trafficking and emigration, famine, imprisonment, disappearances, ...*

*At a time when even the Eritrean regime comes to its senses, and decides to engage with the Ethiopian people to rebuild a common future of peace, unity and prosperity, how is it that the BBC fail to notice it and keep on repeating the same absurdity? When the Eritrean regime reopened the border with the rest of Ethiopia late in 2018, Eritreans gate-crashed border control: in the space of six months, an estimated 300'000 Eritreans had already crossed over, out of a population of less than 2.5 million. The regime has since tried half-heartedly to close back the floodgates, but to no avail.*

*Only a black thread on the map separates now Eritrea from the rest of Ethiopia: on the ground nature is taking its course, and the BBC cannot do anything about it, except perhaps continue in their annual ritual, come what may! Even long after the ultimate peaceful reunification ...*

*Rezene, London.*

---

**የቃላት ፡ መተርጎሚያ**

| ዐጪር ፡ ግስ (ዐማርኛ) | ፎቾ | short glossary (English) | bref glossaire (français) |
|---|---|---|---|
| አህጉር | (ኹለት) ፡ ሀገሮች | (two) countries | (deux) pays |
| አህጉራት | (ብዙ) ፡ ሀገሮች | (many) countries | (plusieurs) pays |
| አህጉራዊ | ወለ ፡ አህጉራዊ<br>በይነ ፡ አህጉራዊ | international | international |
| አገዛዝ | ግዛት | government | gouvernement |
| እግዚእ | ገዢ | sovereign | souverain |
| እግዚእና | ገዢነት | sovereignty | souveraineté |
| እውን | | real, fact | réel, fait |
| እውነት | እውንነት | reality | réalité |
| አካባቢ | | environment | environnement |
| አምሳያ | ምስያ | synonym | synonyme |
| አንድያ | አንድ ፡ ብቻ | unique, sole | unique, seul |
| ብውሕና | | diplomacy | diplomatie |
| በቀርታ | | exception | exception |
| በሐረ | መደረ ፥ ሰፋ ፥ ተን | expand | s'étendre |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

| ዐጪር ፡ ግስ (ዐማርኛ) | ፍቾ | short glossary (English) | bref glossaire (français) |
|---|---|---|---|
| | ጣለለ ። | | |
| ብሔር | ምድር ፡ (ሲ.ወሰን)/ ስፋት ፣ ዓለም | territory / universe | territoire / univers |
| ብሔራዊ | የምድር) | territorial | territorial |
| ብሔራዊ | ዓለም ፡ ዐቀፍ | universal | universel |
| ጋዝ [20] | ንዛኽ | gas | gaz |
| ግዛት | አገዛዝ | government | gouvernement |
| ግለኛ | ባለግል ፥ ሰው | individual (n.) | individu (n.) |
| ግንኙት | ግንኙነት | connection | connexion |
| ጎሳ | ነገድ | tribe | tribu |
| ጕልበት | ኀይል | energy | énergie |
| ደፈር | | highest point | point culminant |
| ደረጃ | | degree | degré |
| ድርስ | | event | événement |
| ሀገራዊ ፡ (ቅጽል) | የሀገር ፡ | citizen | citoyen |
| ሀገራዊ ፡ (ስም) | ባለቤት ፣ ባላገር ፡ (በዓለ ፡ ሀገር) ፣ ዐማራ | citizen | citoyen |
| ወገብጌ | | equator | équateur |
| ውልደት | ትውልድ | nation | nation |
| ዜነኛ | "ጋዜጠኛ" | journalist | journaliste |
| ዞግ ፡ (ዘውግ) | | clan | clan |
| ተንጕባቢ | እንደ ፡ ምድር ፡ በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ የሚንጕበብ ። | planet | planète |
| ሐጋጊ | ሐጋጊ ፡ ሥልጣን | legislative | législatif |
| ሐራ | | independent / free | indépendant / libre |
| ኅዋ | | space | espace |
| ኀይል | | power | puissance |
| ኀይል | | force | force |
| ኀሊ | | idea | idée |
| ጠረየ | | economize | économiser |
| ጥሪት | ሀብት | wealth | richesse |
| ጥርየተኛ | የጥርየትኛ ፡ ባለሚያ | economist | économiste |
| ጥርየት | | economy | économy |
| ይዘት | ይዘታ | régime | régime |
| ከዋኝ | | constituent | constituant |
| ከዋኝ ፡ ጉባኤ | | constituent assembly | assemblée constituante |
| ክዋኔ | ሕገ ፡ መንግሥት | constitution | constitution |
| ኪ.ሜ $^2$ | ኪሎሜትር ፡ ማእዘን | $km^2$ | $km^2$ |
| ኪን | | technique | technique |
| ኪነት | | technology | technologie |
| ኹነት / ኩነት | መንግሥት ፥ የተከወነ ፣ ክዋኔ ፡ ያለው | State | État |
| ልማት | ብልጽግና | development | développement |
| ልዕልና | የበላይነት | supremacy | suprématie |
| መባሕት | | diplomat | diplomate |
| መባሕታዊ | | diplomatic | diplomatique |
| መግበር | መሣሪያ | tool | outil |
| ምድራስ | | university | université |
| መዜንው | | news media | médium d'information |
| ምሕዋር | መንገድ ፣ መኼጃ | circuit | circuit |
| መነሻ | | starting point | point de départ |
| መነሻ | | paragraph | paragraphe |
| መረብ | | network | réseau |
| መርበቢያ | | web site | site internet |
| መርበብት | | internet | internet |
| መርሐ ፡ ሰሜን | | compass | boussole |
| ማወራኛ | መልፈፊያ ፣ ማገናኛ | media | média |
| ምኅዳር | | ecosystem | écosystème |
| መጥሪ/መጥሪት | ጠራዪ/ት | economic agent | agent économique |
| መጥሪት | | capital | capital |
| ምጥራይ | የጥርየት ፡ ሥርዐት | economic system | système économique |
| ምክዋን | | • state system<br>• state apparatus | • système étatique<br>• appareil d'état |
| መኅሊያ | | software | logiciel |
| ማስሊያ | | computer | ordinateur |
| ንዛኽ | ጋዝ ፣ የእንፋሎት ፡ ዐይነት | gas | gaz |
| ነኰርኳር | መገለባበጥ ፥ መለዋወጥ ፤ የሥርዐት ፡ ለውጥ ። | revolution | révolution |
| ንረት | የዋጋ ፡ ንረት | inflation | inflation |
| ሥልጡን | ሥሉጥ | democrat | démocrate |
| ሥሉጥ | ሥልጡን | civil, civic | civil, civique |
| ሥሉጥ ፡ ማኅበር | ሥልጡን ፡ ማኅበር | civil society | société civile |
| ሥልጡንሕዝባዊ | የሥልጡን ፡ ሕዝብ | democratic | démocratique |
| ሥልጡንሕዝብና | ሥልጡንሕዝብነት | democracy | démocratie |
| ሥርዐተ ፡ ፀሓይ | ፀሓይና ፡ ዘጠኙ ፡ ተንጕባቢዎች ፡ አንድ.ጋ | solar system | système solaire |
| ዑደት | ዙር | orbit | orbite |
| ዐማራ | ዐም ፡ ሐራ ፥ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ የኢትዮጵያ | Ethiopian citizenry | ensemble des citoyens |

20 ጋዝ ፤ ከግሪክኛው ፡ "chaos" ፡ የወጣ ፡ ቃል ፤ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ንዛኽ ፡ ለማለት ፡ ሆላንዳዊ ፡ ጥበበኛ ፡ "ጋዝ" ፡ ብሎ ፡ በሆላንድኛ ፡ ላሕይ ፡ የሰመየው ። የ"chaos" ፡ ትርጕም ፡ ከዐማርኛው ፡ "ጋዝ" ፡ ወይም ፡ "ጠብ ፣ ጭቅጭቅ ፣ ውዝግብ" ፡ ጋራ ፡ በምስጢር ፡ ስለሚገጥም ፥ ባማርኛም ፡ "ጋዝ" ፡ ቢባል ፡ ተቃውሞ ፡ አይኖርም ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

| ዐጪር ፡ ግስ (ዐማርኛ) | ፍቾ | short glossary (English) | bref glossaire (français) |
|---|---|---|---|
| | ፡ ሕዝብ | | éthiopiens |
| ዐማራ | ሀገራዊ | citizen | citoyen |
| ዐምሐራ | ዐማራ | citizen | citoyen |
| ፈጻሚ | ፈጻሚ ፡ ሥልጣን | executive | exécutif |
| ፈታሒ | ፈታሒ ፡ ሥልጣን | judiciary | judiciaire |
| ቀረባ | አቀራረብ ፥ ስልት | approach | approche |
| ርትዓዊ ፡ ኹነት | የርትዕ ፡ መንግሥት | State of Right | État de droit |
| ስሕበት | ስበት | gravity | pesanteur |
| ስያስ | ዘዴ | policy | politique |
| ስያሳ | ሥነ ፡ ግዛት ፥ "ፖለቲካ" | politics | politique |
| ስያሳዊ | የስያስ ፡ ወይም ፡ የስያሳ | political | politique (adj.) |
| ስያስኛ | ነገረ ፡ ስያሳ | political science | science politique |
| ትውፊት | ልማድ ፥ ባህል | tradition | tradition |

## የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገሯዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

ማንኛውንም ፡ መልእክት ፥ ለጥቀው ፡ በተዘረዘሩት ፡ የግንኙት ፡ ማማረጫዎች ፥ ለሚመለከተው ፡ ክፍል ፡ ማድረስ ፡ ይቻላል ። እግዚአብሔር ፡ ይስጥልን ።

**መርበቢያ ፡—**

http://www.slttunhzb.net

**የኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እ-ጦማር ፡—**

sh1@ttomar.net

**የሥልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፡ እ-ጦማር ፡—**

sh1@ttomar.net

**ስልክ ፡—**

00 44 74 96 54 15 90 (ብሪታንያ)

| We may be reached alternatively through our: | Nous sommes joignables alternativement par: |
|---|---|
| Web site: | Site Internet: |
| http://www.slttunhzb.net | |
| E-mail: | Courriel: |
| sh1@ttomar.net | |
| Tel: | Tel: |
| 00 44 74 96 54 15 90 (U.K.) | |
| Thank you. | Merci. |



©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።